## በስመ እግዚአብሔር፡ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ።
## በስማ ለእግዝእትነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥ እምነ፥ ወንግሥትነ፡
## ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ወላዲተ አምላክ።
## በኃይለ መስቀሉ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወመድኃኒነ፥ ካህንነ፥ ወንጉሥነ፡
## ኢየሱስ ክርስቶስ።

## ተፈጸመ ትስብእት፡ በኢትዮጵያ ማርያም ድንግል!
## በብሥራተ ቅዱስ ገብርኤል፡ ዜናዌ ቃል!

ይድረስ፡- በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ክህነታዊ ባልደረባዬ ለኾንኸው፡ ለተወደድህና ለተከበርህ ኪዳናዊ ወንድሜ ፈቃደ-ሥላሴ።

ኅዳር ፴ ቀን፥ ፳፻፲ ዓመተ ምሕረት የጻፍህልን ደብዳቤ፡ በእ-ጦማርህ አማካይነት ደረሰን፤ እግዜር ይስጥልን!

በመንፈስ ቅዱስ መርሕ የተጻፈው፡ ይኸው መልእክትህ፡ ከተናፋቂው ቤተሰብህ ጋር፡ ደኅና መኾናችሁን ስላበሠረን፡ ደስ ብሎን፡ እኛንም፡ እንደእናንተው፡ በያለንበት፡ በደኅንነት የሚጠብቁንን፡ እግዚእነ ኢየሱስ መሢሕንና ቅድስት ድንግል እናቱን፡ እግዝእትነ ማርያምን አመሰገንን።

ኪዳናዊ ወንድሜ ሆይ!

፩. ምናልባት፡ ለአንተ፡ ገና አልታወቀህ እንደኾነ እንጂ፡ ይህንና የቀደመውን፥ ሌሎቹንም፡ የበፊቶቹን ደብዳቤዎችህንና ጽሑፎችህን እንድታዘጋጅ፥ ጥያቄዎችንም እንድታቀርብልኝ የሚያደርግህ፡ ማን መሰለህ? የሥላሴን ፈቃድ ፈጻሚ ከኾንኸው፡ ከአንተ ጋር፥ በአንተም ዐድሮ የሚሠራው፡ አሳሳቢውና አነቃቂው፥ አነሣሹና አስፈጻሚው እኮ፡ መንፈስ ቅዱስ ነው።

ይኼም የኾነውና የሚኾነው፡ ለአንተ ብቻ ሳይኾን፥ በአንተ አማካይነት፡ መለኮታዊው ጥሪ ለተላለፈላቸው፡ ለሌሎች ሰብኣውያን ወገኖች ኹሉ፥ ለወገኖችህ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ጭምር፡ የዘለዓለማዊው መልካም ሕይወት ባለቤቶች የመኾንን ጸጋ ለመቀበል እንዲበቁና እንዲታደሉ የሚያስችላቸውን እውቀት ሊያበረክታቸው መኾኑን፡ በእምነት አረጋግጬ መናገሩ ይቻለኛል።

ስለዚህ፡ አንተም፡ ለዚህ ተልእኮ፡ ራስህን፡ በፈቃደኛነት በማቅረብህ፡ ደስ ሊልህና ልትረካ ይገባሃል። እኔም፡ "እንኳን ደስ አለህ!" እያልሁ፡ የበኩሌን ምርቃት አቀርብልሃለሁ።

ይህን የመሰለውን የአስተያየትና የማብራሪያ፥ የጥያቄና የመልስ ልውውጣችንን የሚከታተሉና የሚመለከቱ ኹሉ፡ እየራሳቸውን፡ በአንተ ቦታ አስገብተውና ተክተው፡ በዚህ፡ የመንፈስ ቅዱስን እውቀት፡ እየራሳቸውን እንደሚያጐለምሱ፡ ተስፋ ማድረግ ብቻ ሳይኾን፡ አምናለሁ።

፪. በመጨረሻ በላክሁልህ ማብራሪያ ውስጥ፡ "በስሕተትና ባለማወቅ፥ ያለፈቃድ ተገድዶና ተታልሎ፥ ወይም፡ ሳያውቁ፡ በድንገተኛና በገነፈለ ስሜት፡ የሚፈጸመው ጥፋት፡ በደል፥ ወይም፡ ኃጢአት አይደለም። ይህ እውነታ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀርቶ፡ ሰዎች እንኳ፡ "ፍትሕ ርትዕ" ብለው በሚያካኺዱት ሥርዓታቸው፡ ሲሠሩበት ይታያል።" የሚለውን አንቀጽ መነሻ በማድረግ፡ ላቀረብሃቸው ጥያቄዎችህ፡ የምሰጥህ ማብራሪያ፡ እንደሚከተለው ይኾናል፡-

አ. ለዚህ ማብራሪያዬ፡ በአንተ በኩል የሰጠኸው ትርጕም፡ በእኔ በኩል ሠርዖ ከገለጽሁትና ካስተላለፍሁት አሳብ ጋር፡ የተስማማና የተዛመደ አይደለም። እንዲያውም፡ ተቃራኒው ነው። ምክንያቱም፡ አንተ ባቀረብሃቸው፡ በእነዚያና እነርሱን በመሰሉት ሰዎች ዘንድማ፥ ወንዶች ኾኑ ሴቶች፡ "አድርገውታል!" ወይም፡ "ያደርጉታል!" ያልካቸው የድርጊቶች ዓይነቶች ኹሉ፡ "በስሕተትና ባለማወቅ፥ ያለፈቃድ ተገድዶና ተታልሎ፥ ወይም፡ ሳያውቁ፡ በድንገተኛና በገነፈለ ስሜት" የተፈጸሙ፥ ወይም፡ የሚፈጸሙ ሳይኾኑ፥ ነገር ግን፡ የእነዚህ ኹሉ እውነተኛ ባሕርያት፡ ተቃዋሚ በኾኑት፡ "በድፍረትና በማወቅ፥ በራስ ፈቃድና ፍላጎት፥ ምርጫና ውሳኔ፡ ውዴታና ስምምነት፥ በቅድሚያ ታስበውና ታቅደው፥ ዝግጅትም ተደርጎባቸው፡" የተፈጸሙ፥ ወይም፡ የሚፈጸሙ መኾናቸውን፡ ራሱ፡ የአቀራረብህ መልክና ይዘት ያመለክታል።

እንዲያ የመኾኑን እውነታማ፡ በእያንዳንዱ ፍጡሩ ዘንድ፡ የታሰበውን ቀርቶ፡ በራሱ፡ በአሳቢው ዘንድም፡ ገና የማይታወቀውን፡ የወደፊት አሳብ ኹሉ እንኳ፡ አስቀድሞ የሚያውቀው፡ የፈጣሪ መንፈስ ብቻ ሳይኾን፡ የዚያ የአድራጊው ሰው ኅሊናም፡ በግልጽ ይመሰክራል።

ስለዚህ እኮ ነው፡ "በስሕተትና ባለማወቅ፥ ያለፈቃድ ተገድዶና ተታልሎ፥ ወይም፡ ሳያውቁ፡ በድንገተኛና በገነፈለ ስሜት፡ <u>የሚፈጸመው ጥፋት፡ በደል፥ ወይም፡ ኃጢአት አይደለም። ይህ እውነታ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀርቶ፡ ሰዎች እንኳ፡ "ፍትሕ ርትዕ" ብለው በሚያካኺዱት ሥርዓታቸው፡ ሲሠሩበት ይታያል።"</u> ያልሁት። እንኳንስ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች እና የኢትዮጵያ ልጆች" በኾኑት፡ በኪዳናውያትና በኪዳናውያን ዘንድ ቀርቶ፡ "የሰው ልጆች እና የክፋት ልጆች" በኾኑት፡ በሰብአውያን ፍጡሮች ዘንድ እንኳ፡ "ስሕተትና አለማወቅ፥ ያለፈቃድ መገደድና መታለል፥ ወይም፡ ድንገተኛና የገነፈለ ስሜት" ምን እንደኾነ ታውቆ፡ "የሕግ ዳኝነትን፡ በትክክል እንሰጣለን!" ይሉ የለምን? አዎን ይላሉ፤ ይህንም ቃላቸውን፡ በሕግ መጽሓፎቻቸው ውስጥ ሳይቀር፡ ይመዘግባሉ፤ በአዋጅም ያወጣሉ።

ለመኾኑ፡ "ስሕተትና አለማወቅ፥ ያለፈቃድ መገደድና መታለል፥ ወይም፡ ድንገተኛና የገነፈለ ስሜት" ምን ማለት ነው? የእነዚህ ቃላት፡ የእያንዳንዳቸው ትርጓሜ፡ ምን እንደኾነ፥ ወይም፡ እነዚህ ኹኔታዎች፡ ምን እንደኾኑ፡ ማብራሪያቸው፡ በዓለማውያኑና በሥጋውያኑ ሰብአውያን ፍጡሮች ዘንድ ያለውና በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ ያለው፡ እርግጥ የተለያየ ሊኾን ይችላል።

ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ እኔ፡ በዚያ፡ በቀደመው፡ የማብራሪያ መልሴ ውስጥ፡ እንደገና መተርጐም፥ ወይም፡ ማብራራት ያስፈልገኝ ኖሮዋልን? አይመስለኝም። ምክንያቱም፡ ስሕተት፡ ስሕተት መኾኑ፥ አለማወቅ፡ አለማወቅ መኾኑ፥ ያለፈቃድ መገደድ፡ ያለፈቃድ መገደድ መኾኑ፥ መታለል፡ መታለል መኾኑ፥ ድንገተኛና የገነፈለ ስሜትም፡ ድንገተኛና የገነፈለ ስሜት መኾኑ፡ እንኳንስ፡ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት ዘንድ ቀርቶ፡ በዓለማውያኑና በሥጋውያኑ የሕግ ምሁራን ዘንድ ሳይቀር፡ ተገቢ ትርጉሙ፡ በጥንቃቄ ተተንትኖና ታውቆ፡ ለትክክለኛ የፍርድ ውሳኔ ተመቻችቶ እንደሚሠራበት፡ በማንም ዘንድ የሚታወቅ ነው።

በ. እዚህ ላይ፡ ሊጤን የሚገባው ቍም ነገር አለ፤ ይህም፡ በኪዳናውያትና በኪዳናውያን ዘንድ፡ "**ማወቅ**"፥ ወይም "**እውቀት**" የምንለው ረቂቅ ዘይቤ፡ ብርሃን የኾነውንና በእግዚአብሔር እውነት ላይ የተመሠረተውን መለኮታዊዉን እንጂ፡ "ባዶነት" የኾነውንና በሰይጣን ሓሰት ላይ የተመሠረተውን፡ የሰውኛውን አለመኾኑ ነው፤ ልክ፡ "እውነተኛነት፡ ወይም፡ እውነት" ስንል፡ "እውንና መልካም"፥ እንዲሁም፡ "ሕይወት" የኾነችውን፡ የእግዚአብሔሯን እንጂ፡ "ምትሓትና ክፉት፥ ሞትም" የኾነውን፡ የሰውኛውን፥ ወይም፡ ሰይጣናዊውን "ሓሰትን" ማለታችን እንዳልኾነ ኹሉ ማለት ነው።

ገ. በዚህ መሠረት፡ "**መሳሳት**"፥ ወይም፡ "**ስሕተት ማድረግ**" ምን እንደኾነ ለማወቅ፡ በኪዳናውያትና በኪዳናውያን ዘንድ ሳይቀር፡ ኹልጊዜም ባይኾን እንኳ፡ አልፎ አልፎ፡ ስሕተት የማያደርግ ሰብአዊ ፍጡር ባለመኖሩ፡ እውነታውን፡ በቀላሉ፡ ለራስም፡ ለመረዳት፥ ለሌላውም፡ ለማስረዳት አያዳግትም። ያም ስሕተት አድራጊ፡ እውነተኛ ከኾነ፡ ሳያውቅ ለፈጸመው፡ ለዚያ ስሕተቱ፡ "አዝናለሁ! ተሳስቼ ነው!" ብሎ፡ በዚያ ስሕተት የተጎዳውን ሰው፡ ይቅርታን የማይጠይቅ አለን? ያለ አይመስለኝም።

ስለዚህ፡ "**ስሕተት**" የሚባለው የተግባር ዘይቤ፡ በልማዳዊው አነጋገር፡ "ሳያውቁ፥ ወይም፡ ባለማወቅ የሚያደርጉት እንጂ፡ አውቀው፥ ወይም፡ በማወቅ የሚፈጽሙት ድርጊት አይደለም!" ቢባልም እንኳ፡ ራሱ፡ "ስሒት"፥ ማለት፡ "ከእውነት ወጥቶ መሳት"፥ ደግሞም፡ "እያወቁ ክፉ ማድረግ" ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ በመኾኑ፡ ባሕርዩ፡ ጥፋት እንጂ፡ ልማት፥ ክፉ እንጂ መልካም ስላይደለ፡ እነሆ፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ ይቅርታ ይጠየቅበታል።

ደ. እንደዚሁ ኹሉ፡ ስለ"**አለማወቅ**"፡ በቀላሉ፡ ለራስም፡ ለመረዳት፥ ለሌላውም፡ ለማስረዳት ይቻላል፤ ይኸውም፡ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት ዘንድ ሳይቀር፡ በየጥቃቅኑ፡ የሥጋዊና የነፍሳዊ፥ የመንፈሳዊም ህልውናችን ረገድ፡ ብዙ የማናውቃቸው፡ የገሃድና የምሥጢር ነገሮች በመኖራቸው ነው። ይኹን እንጂ፡ በዚህ ረገድ ያለውን፡ የቃሉን ትርጓሜ፡ እጅግ በረቀቀውና በጠለቀው መጠን፡ አስተውለው ሲመለከቱት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል መከራው ላይ ሣለ፡- "አባ! ስረይ ሎሙ! እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ።"

ማለትም፡ "አባት ሆይ! የሚያደርጉትን አያውቁምና፤ ይቅር በላቸው!" ብሎ፡ ስለሚያሠቃዩት ገዳዮቹ አላዋቂነት የተናገረው ቃል፡ ለዚህ እውነታ በቂ ማረጋገጫ ይኾናል።

እርሱ ጌታችን፡ በኀዘኔታና በይቅር ባይነት፡ "የሚያደርጉትን አያውቁም!" ይበል እንጂ፡ በእነርሱ፡ በሰቃዮቹ አይሁድ ዘንድ ግን፡ "እኛ፡ አንተ ከምታውቀው በላይ፡ የምናውቅ ኾነን ነው፡ ይህን ኹሉ እያደረግንብህ ያለነው!" እያሉት እንደነበረ፡ በአድራጎታቸው ኺደትና ውጤት፡ በግልጽ ታይቷል። (ሉቃ. ፳፫፥ ፴፬።)

ይኹን እንጂ፡ በሰዎች ልቦና ውስጥ ያለውን፡ ረቂቅና ጥልቅ አሳብ የሚያውቀው፡ እርሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ በዚህ ረገድ ባለው መለኮታዊ እውቀቱ መሠረት፡ የእነርሱን አላዋቂነት አውቆ፡ ይህን ቢልም እንኳ፡ እነርሱ ግን፡ እየራሳቸውን፡ ከእርሱ የበለጠ እንደሚያውቁ አድርገው፡ ምንም በደል የሌለበትን፡ ፍጹም ንጹሕ የኾነውን እርሱን፡ እስከመስቀል ሞት በሚያደርስ የፍርድ ቅጣት፡ አሠቃይተው መግደላቸው፡ በእርሱ ዘንድ፡ እንደአላዋቂነት የተቈጠረው እውቀታቸው፡ የበቀል ጥላቻን የተመላ፡ የክፋት መገለጫ መኾኑን፡ በይፋ አረጋግጠዋል።

እዚህ ላይ፡ ስለአላዋቂነት ከተነሣ ዘንድ፡ እስኪ፡ ጥቂት ልበል! ለመኾኑ እኛ፡ እያንዳንዳችን፡ የሩቆቹን ትተን፡ ከባልና ሚስት፥ እንዲሁም፡ ከወላጆችና ልጆች በመጀመር፡ እስከእየራሳችን ድረስ ባለን ቅርበት፡ አንዳችን፡ አንዳችንን፡ "አውቀዋለሁ! አውቃታለሁ!" ብለን በማረጋገጥ ለመናገር የምንደፍር፡ ስንቶቻችን ነን? በመካከላችን እንዲገኝ፡ በእውነት በምንፈቅድለት፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከኾነውና ከሚኾነው በቀር፡ እርስ በርሳችን አለመተዋወቃችንን እንጂ፡ "እንተዋወቃለን! ተዋውቀናልም!" ብለን፡ በእርግጠኝነት ለመናገር የምንችልበት፡ መብቱም፥ ሥልጣኑም፥ ኃይሉም የለንም።

እንግዴህ፡ ኪዳናዊ ወንድሜ ሆይ! እነዚሁ አይሁድ፡ እንዲህ፡ ይፋ ባደረጉት አዋቂነታቸው፡ የግፍ ጭካኔና የዕብሪት ድንፋታ በተመላበት ድፍረት የፈጸሙትን በደል፡ በእርሱ ዘንድ እንዳላዋቂነት ቈጥሮ፡ በሰውነቱ ይቅርታን ጠይቆ፥ በእግዚአብሔርነቱም ይቅር ብሎ፡ ማለትም፡ ራሱ አማላጅና ተማላጅ ኾኖ፡ ዕርቅንና ሰላምን፡ በፍጹም የፍቅር ቤዛነት፡ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ፡ በዳዩን ሰውንና ተበዳዩን እግዚአብሔርን  እንዴት እንዳስታረቀ ተመልከተው!

ከዚህ እውነታ ለመድረስ፡ አይሁድ፡ "የለም! ይህን ኹሉ ግፍና በደል፡ በአንተ ላይ የምናደርገው እኮ፡ **አውቀን ነው!**" እያሉትና እያሠቃዩት፥ እየተሣለቁበትም ሣሉ እንኳ፥ እነርሱ፡ ንስሓ ሳይገቡ፥ **ይቅርታም** ሳይጠይቁት፡ እርሱ፡ መድኃኒታችን ግን፡ በበኩሉ፡ ወደርና ወሰን በሌለው መሓሪነቱ፡ "**የለም! ይህን ኹሉ ግፍ፡ በእኔ ላይ እየፈጸማችሁት ያላችሁት፡ ሳታውቁ ነውና፡ ይቅር ብያችኋለሁ!**" ያለበትን ኹኔታ፡ በቅድሚያ፡ በአንድ ወገን ታስቀምጠዋለህ።

በሌላው ወገን ደግሞ ቀጥለህ፡ ይህን ኹኔታ፡ አንተ፡ ዘርዝረህ ካቀረብሃቸው፡ የሰዎች የአጥፊነትና የእምቢተኝነት፥ የኃጢኣተኝነትና የክፉነት ኹኔታዎች ጋር ታስተያየዋለህ፤ ታመሳስለዋለህ፤ ታመዛዝነዋለህ፤ ታነጻጽረውማለህ።

ታዲያ! በዚህ ጊዜ፡ የምታገኘው ውጤት፡ ከቶ ምን ይመስልሃል? በመለኮታዊው የምሕረት ልግሥናና በአንተ የፍርድ ሚዛን መካከል ያለው ልዩነት፡ የቱን ያህል የተራራቀ እንደኾነስ ታስተውለዋለህን? ይህን እውነታ፡ አኹን በደረስህበት፡ በዚህ ኪዳናዊነትህ፡ ልትገነዘበው የምትችል ይመስለኛል። ካልቻልህም፡ ከዚህ ያደረስኸውን ገድልህን ቀጥልበት! ከዚያ እውነታ ያደርስሃል።

ሀ. ፈጣሪያችን፡ ለዚህ፡ ውለታቢስና ተቃዋሚው ኾኖ ለተገኘው ፍጡሩ፡ ያለውን ፍጹም ፍቅርና ይቅር ባይነት በሚመለከት፡ ሓዋርያው፡ እንዲህ ሲል የጻፈው ቃል፡ ከዚህ ርእሰ ነገር ጋር አግባብነት ስላለው፡ እዚህ ላይ ጠቅሼዋለሁ፡- "ወሶበ እንዘ ፀሩ ንሕነ ለእግዚአብሔር፡ ተሣህለነ በሞተ ወልዱ፤ እፎ እንከ ይሣህለነ ፈድፋደ፡ እምከመ ተዐረቀነ፥ ወተሣህለነ፡ ያሐይወነ፡ በሕይወተ ወልዱ።

ማለትም፡ " እኛ፡ የእግዚአብሔር ጠላቶቹ ኾነን ሣለን፡ በልጁ ሞት፡ ይቅር ካለን፡ ታዲያ! እንዲህ በታረቀንና በማረን፥ ሕያዋንም ባደረገን፡ በልጁ ሕይወትማ፡ እንዴት፡ በበለጠ ይቅር አይለን!?" (ሮሜ. ፭፥ ፲።)

እንግዴህ፡ የእርሱ የሰማዩ አባታችንና የእርሷ የሰማይዋ እናታችን ፈቃድ፡ የእኛ፡ የልጆቻቸው አሳባችን፥ ንግግራችንና ምግባራችን፡ እንደዚህ፡ እንደእርሱ፥ እንደልጃቸው እንዲኾን መኾኑን አንዘንጋ!

ይኸው፡ መለኮታዊውና ትስብእታዊው ልጃቸው፡ ኢየሱስ መሢሕ፡ ኦሪታውያኑ አይሁድ፡ ስለአሥሩ የእግዚአብሔር ቃላት፡ የሰጡትን የተሳሳተ ትርጓሜ በመንቀፍ፡ እውነተኛውን አምላካዊ መልእክት፡ ላመኑበትና ለተከተሉት ወዳጆቹ፡ የእነዚህኑ ቃላት፡ ትክክለኛ ምንነት፡ አብራርቶ ከገለጸላቸው በኋላ፡ በመጨረሻ የሰጣቸው ማጠቃለያ መመሪያ፡ "አንትሙሰ፡ ኩኑ ፍጹማነ፤ ከመ አቡክሙ ሰማያዊ፡ ፍጹም ውእቱ!"

ማለትም፡ "እንግዴህ፡ የሰማዩ አባታችሁ፡ ፍጹም እንደኾነ፡ እናንተም፡ እንደርሱ፡ ፍጹማን ኹኑ!" የሚል እንደኾነ ታውቀዋለህ።

ይህም፡ በኦሪቱ፡ "ሰማዕክሙ ዘተብህለ፡ ለቀደምትክሙ፡- 'አፍቅር፡ ቢጸከ! ወጽላእ፡ ጸላኢከ!' ወአንሰ እብለክሙ፡- 'አፍቅሩ፡ ጸላእተክሙ! ባርክዎሙ፡ ለእለ ይሰድዱክሙ! ሠናየ ግበሩ፡ ለእለ ይጸልኡክሙ! ወጸልዩ፡ በእንተ እለ ይትዔገሉክሙ! ከመ ትኩኑ ውሉዶ፡ ለአቡክሙ ዘበሰማያት፤ እስመ ውእቱ ያሠርቅ ፀሓየ፡ ላዕለ ኄራን፥ ወእኩያን፤ ወያዘንም ዝናመ፡ ላዕለ ጻድቃን፥ ወኃጥኣን።"

ማለትም፡ "ከእናንተ ለቀደሙት፡- 'ባልንጀራህን ውደድ! ጠላትህንም ጥላ!' እንደተባለ ሰምታችኋል፤ እኔ ግን፡ እላችኋለሁ፡- 'በሰማያት ለለው አባታችሁ፡ ልጆች ትኾኑ ዘንድ፡ ጠላቶቻችሁን፡ ውደዱ! የሚያሳድዷችሁንም፡ መርቁ! ለሚጠሏችሁም፡ መልካም አድርጉ! ለሚቃወሟችሁም ጸልዩ!" በሚለው ቃሉ የተደመደመው ነው። (ማቴ. ፭፥ ፲፯-፵፰።)

ወ. በስቅለት መከራው፡ ክፋትን፥ ሓሰትን (ኃጢኣትን) እና ሞትን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ባስወገዳቸው ቤዛችን፡ በኢየሱስ መሢሕ እና በሰቃዮቹ አይሁድ መካከል፡ ስለማወቅ እና ስለአለማወቅ የነበረው፡ የዚያ ኹሉ ያለመግባባቱ **ችግር**፡ መነሻውም፥ መድረሻውም፡ አንድና አንድ ብቻ ኾኖ ቀጥሏል፤ ያም ችግር፡ በዚያን የስቅለቱ ጊዜ፡ በአንድ ወገን፡ በዓለሙ መድኃኒት ዘንድ የነበረው አስተሳሰብ እና በሌላው ወገን ደግሞ፡ የግፍ በደላቸውን አውቀው በሚፈጽሙት አይሁድ ዘንድ የነበረው አስተሳሰብ፡ ጨርሶ የተለያየ በመኾኑ ነው።

ይኸውም፡ እርሱ ጌታችን፡ የሚያስበውና የሚናገረው፥ የሚያደርገውና የሚደርስበትን ኹሉ የሚቀበለው፡ በመጨረሻው የመንፈስ ብቅዓቱ ሲኾን፡ እነርሱ ግን፡ የሚያስቡትና የሚናገሩት፥ የሚያደርጉትና በእርሱ ላይ በጭካኔ የሚያካኺዱትን ግፍ ይፈጽሙ የነበሩት፡ በሥጋዊው የአስተሳሰብ ደረጃ ስለኾነ፡ እርሱ የሚለውንና እያደረገ ያለውን ምግባር አውቀው ለመቀበልና ለመፈጸም የማይቻላቸው ኾነ።

ያለመግባባቱ ጠንቅ፡ በኹለቱም ወገኖች መካከል የነበረው፡ በማናቸውም መሥፈርትና ሚዛን፡ ሊታረቅና ሊስማማ ቀርቶ፡ ሊቀራረብና ሊተያይ እንኳ የማይቻለው፡ የአስተሳሰባቸው ልዩነት እንደነበረ፡ ሊታወቅ ይገባል። ይኸውም፡ የእነርሱ፥ የአይሁድ፡ ፍጹም ሥጋዊነትና የእርሱ፥ የመሢሕ ኢየሱስ፡ ፍጹም መንፈሳዊነት ነው።

ያ፡ በተሰቀለው ጌታ የተነገረውና እየኾነ የነበረው እውነታ ኹሉ፡ በእነርሱ፡ በሰቃዮቹ አይሁድ ዘንድ፡ ሊታወቅና ሊቀበሉት ይቻላቸው የነበረው፡ እየራሳቸውን፡ ወደመንፈሳዊው የእውቀት ብቅዓት ደረጃ ከፍ ማድረግ ሲቻላቸው ብቻ ነበር፤ ነውም። ይህ **ችግር፡** ዛሬም፡ እነርሱን በመሰሉት ኦሪታውያንና ሥጋውያን ዘንድ፥ በአንተ ጽሑፍ ውስጥ ሳይቀር፡ እየተንጸባረቀ ይታያል።

በዚህ፡ በጌታ በኩል በተፈጸመው እውነታ አንጻር፡ ሰዎች፥ የጌታችን ደቀ መዛሙርት እንኳ ሳይቀሩ፡ ከዚህ የርኅራኄና የምሕረት ምግባር፡ የቱን ያህል የራቁ መኾናቸውን ለማሳየት፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ ወደኢየሩሳሌም ሲጓዝ፡ በአንዲት የሳምራውያን መንደር በኩል አልፎ እንዳይኼድ፡ መንደረተኞቹ በከለከሉት ጊዜ፡ ከሓዋርያት መካከል፡ ኹለቱ ወንድማማቾቹ፡ ያዕቆብና ዮሓንስ፡ **"እግዚኦ! ትፈቅድኑ ንበል፡ 'ይረድ እሳት እምሰማይ፤ ወያጥፍአሙ፡ በከመ ገብረ፡ ኤልያስ!'"**

ማለትም፡ **"ጌታ ሆይ! ኤልያስ እንዳደረገ፡ 'ከሰማይ፡ እሳት ወርዶ ያጥፋቸው!' እንል ዘንድ ትፈቅዳለህን?"** ብለው ላቀረቡለት ጥያቄ፡ ወደእነርሱ ዘወር ብሎ፡ በሌላ መንገድ እንዲኼዱ ከማዘዝ ጋር፡ በግሣጼ ቃል የሰጣቸውን፡ እንዲህ የሚለውን መልሱን፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ፡ ለማስረጃነት ይበቃል፤ ይኸውም፡ **"ኢተአምሩኑ፡ በአይ መንፈስ አንትሙ? እስመ ኢመጽአ ወልደ ዕጓለ እመሕያው፡ ከመ ያጥፍእ ነፍሳተ፣ ዘእንበለ ከመ ያሕዩ።"**

ማለትም፡ "ይህን ስትሉ፡ በምን ዓይነቱ መንፈስ እንደኾናችሁ፡ አላወቃችሁምን? እኔ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እኮ፡ የማርያም ልጅ ኾኜ፡ ወደዚህ ዓለም የመጣሁት፡ የሰዎችን ነፍሳት ላድን እንጂ፡ ላጠፋ አይደለም።" (ሉቃ. ፱፥ ፶፬-፶፭።)

አዎን! ያ፡ "ችግር"፡ ዛሬም፡ በብዙዎች ዘንድ፡ በአንተም ጽሑፍ ውስጥ ተንጸባርቆ እንደሚታየው፡ እንዲህ፡ በምትሓትነት እየተከሠተ፥ ደግሞም፡ "ይህን ኹሉ የይቅር ባይነት ርኅራኄና የምሕረት ቸርነት ማድረግ፡ እንዴት ይቻላል? መኾንም፡ የለበትም!" እያለ፡ ይህችኑ፡ ወላዋይና ተጠራጣሪ የኾነችውን፡ ምስኪኗን ሰብኣዊት ነፍስ፡ ሲያስቸግራት ኖርዋል፤ እርሷም፡ ከድክመትና ከስንፍና፥ ከወረተኛነትና ከግብዝነት ዝንባሌዋ የተነሣ፡ መንፈሳዊው አካሏና ባሕርይዋ፡ የሚያሳስባትን "እንቢ!" ብላ፡ ለእርሱው፡ ለሥጋዊው ኃይል እያጎበደደች ያለችው እኮ፡ በዚሁ፡ በሥጋዊው አካላችንና ባሕርያችን ድክመትና ስንፍና ምክንያት መኾኑ፡ በግልጽና በእርግጥ ሊታወቅ ይገባል። ይኸው እውነታ ታውቆ፡ እያንዳንዱ ግለሰብ፥ ወንድ ኾነ ሴት፡ ራስን፡ ሳይመኽ፡ በብርሃኑ፡ ለዚሁ፡ ለመንፈሳዊው አካልና ባሕርይ ደረጃ ማብቃቱ አግባብና ጠቃሚ ይኾናል።

ይኸው "ችግር"፡ ጥንቱኑም፡ በፍጥረት ጊዜ፡ ያልተፈጠረ በመኾኑ፡ ያልነበረ ሲኾን፡ ይህን አልቦነት [ባዶነት]፡ ከፍጥረት በኋላ፡ በቅድሚያ፡ "የእግዚአብሔር መልአክ" ተብሎ፡ በመንፈሳዊ ረቂቅነት ብቻ የተፈጠረው ዲያብሎስ፥ ከእርሱ ተከትሎም፡ "የእግዚአብሔር ልጅ" ተብሎ፡ በሥጋዊ ሰውነት ጭምር የተፈጠረው አዳም፡ እነዚህ፡ ኹለት ዓይነት ፍጡራን፡ እየራሳቸውን፡ "ክፋት" ወደተባለው፡ ወደፀረ-እግዚአብሔርነት በመለወጥ፡ በምትሓትነትና በሓሰትነት፥ በኃጢአትነትና በመዊትነት እንዳመጡት ይታወቃል። ይኹን እንጂ፡ ይህ ኹኔታ ቢደርስም እንኳ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ "መድኃኔ ዓለም" የኾነው ኢየሱስ መሢሕ፡ ከላይ በተገለጸው ኹኔታ፡ ያን "ችግር"፥ ያን "ክፋት"፡ ወደቀደመው "ባዶነቱ" በመመለስ፡ ያስወገደው መኾኑ፡ ታውቋል፤ ተረጋግጧልም።

ዘ. "መገደድ" ራሱ፡ "ያለፈቃድ" የሚለው ቅጽል እንኳ ሳያስፈልገው፡ በራሱ፡ የቃልነት ትርጓሜው ብቻ፡ የሚገልጸው እውነታ አለ። ይኸውም፡ ግለሰቦች፡ ሴቶችም ኾኑ ወንዶች፡ አንድን ነገር፡ ሳይስማሙበት፡ የሥጋዊ አካላቸውን፥ የነፍሳዊ አእምሮአቸውንና የመንፈሳዊ እምነታቸውን፡ ተፈጥሮአዊና መለኮታዊ ጸጋና ክብር፥ መብትና ንጽሕና፡ በሚጎዳ መልክና ይዘት፡ መቋቋም በማይቻላቸውና ከዓቅማቸው በላይ በኾነ የጕልበት ኃይል በመጠቀም፡ ያን ክፉና ሕገወጥ ተግባር፡ ያለፍላጎታቸውና ያለፈቃዳቸው፡ ተገድደው እንዲፈጽሙት፥ ወይም፡ እንዲፈጸምባቸው የተደረገበትን ኹኔታ የሚያሳይ በመኾኑ ነው። ለዚህ አስረጅነትም፡ በሴት፥ ወይም፡ በወንድ ላይ ሊደርስ የሚችለውን፡ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን፡ እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

ሐ. "መታለል"ም እንዲሁ፡ መገደድ በሌለበት ኹኔታ፥ ነገር ግን፡ በዚያ ቦታ፡ አእምሮን የሚነሳ መድኃኒትን በመስጠት፥ ወይም የሚያሰክር መጠጥን አጠጥቶ፡ ናላን በማዞር፥ ወይም በትምህርት መልክ ኾነ በምትሓታዊ ፈሊጥ፡ ሓሰቱን፡ እውነት አስመስሎ ማቅረብ ነው።

ይህንም ውጤት፡ በሰብአዊው አንጎል ላይ እንዲቀረጽ በማድረግ፡ ግለሰቦች፡ ሴቶችም ኾኑ ወንዶች፡ ክፉና ሕገወጥ የኾነን አንድን ነገር፡ "ተቀብለነዋል! አምነንበታልም!" ከሚሉበት ሓሳዊ እውቀት የማድረስ ኹኔታን የሚያሳይ ነው።

ለዚህ ዘይቤ እውነተኛነት፡ የቀደመውን፡ የዚህን ዓለም ሰዎች ታሪክና ዛሬ፡ በመላው ዓለም ላይ፡ ጥቂቶች ብልጦች፡ "ሕዝባዊ ሥርዓት፥ ቤተ ሃይማኖትና ቤተ መንግሥት" እያሉ ባቋቋሟቸው ድርጅቶቻቸው አማካይነት፡ "መደዴ" በሚሉት፡ በአብዛኛው ሰብአዊ ፍጡር ላይ፡ እያካኼዱ ያሉትን፡ የአገዛዝ አመራርና አስተዳደር፡ እንደማስረጃ ማቅረብ አያዳግትም።

ጠ. እየራሳቸውን፡ ለመንፈሳዊው የፍጹምነት ደረጃ ያበቁ፡ ኪዳናውያን ወንዶችና ኪዳናውያት ሴቶች ካልኾኑ በቀር፡ "ድንገተኛና የገነፈለ ስሜት"፡ በሥጋዊው የእውቀትና የሕይወት ደረጃ በሚኖረው፡ በማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ላይ የሚደርስ፥ ሊወገድም የማይቻል፡ የተፈጥሮ ጠባይ መኾኑ፡ በኹሉ ዘንድ የታወቀ ነው።

የዚህን መድበል ቃል ምንነት ለመግለጽ፡ ንዴትንና ቍጣን፥ ብስጭትንና ጭንቀትን፥ ድንጋጤንና ፍርኀትን፥ ኀዘንንና ልቅሶን፥ አደጋንና ድንገተኛ ጥቃትን ለመከላከል፡ የአልሞት-ባይ- ተጋዳይነት ግዳጅን የመፈጸም ቍርጠኛነትን፥ የአካል ስንኵልነትንና የጤና ጒድለትን፥ የአእምሮ ቀውስንና የመሰሉትን የተፈጥሮ ጠባያትና ሣንኮች፡ በምሳሌነት መጠቃቀስ ይቻላል።

እንግዴህ፡ እነዚህን ኹኔታዎች ነው፡ የሥጋና የዓለሙ ተገዦች የኾኑት የሰው ወገኖች፡ ከፈጣሪ፡ በተፈጥሮ ባገኙት፡ ሰብአዊ እውቀታቸው ተመርተው፡ በሕጋቸው፡ ማናቸውንም፡ ጥቃቅን ኾነ ከባድ ወንጀልን የፈጸሙ ሰዎች ኹሉ፡ "ጥፋተኞች ናቸው!" ተብለው፡ የፍርድ ቅጣት እንዲወሰንባቸው ከመደረጉ በፊት፡ ያን ጥፋት፥ ወይም፡ ወንጀል፡ በምን ዓይነት ኹኔታና አካባቢ እንደፈጸሙት በትክክል ለማወቅና ለመረዳት፡ እነዚያን፡ ከላይ የተዘረዘሩትን ኹኔታዎች መሠረት በማድረግ፡ ብርቱ ምርመራና ማጣራት የሚያካኺዱት። በበቂ ማስረጃና ምስክርነትም፡ እውነቱ፡ እንዲረጋገጥ የሚያደርጉት።

ይህ ኹሉ የማጣሪያ ምርመራ ከተደረገ በኋላ፡ የምርመራውና የማጣራቱ ውጤት፡ ከእነዚህ፡ ከምንወያይባቸው ኹኔታዎች መካከል፡ አንዱ ምክንያታዊ እንከን፡ በጥፋተኛው፥ ወይም፡ በወንጀለኛው ላይ የተገኘ እንደኾነ፡ ያ ሰው፡ እንደነገሩ ክብደትና ቅለት፡ ወይ፡ ከጥፋቱ ነጻ ኾኖ፡ ያለቅጣት ይለቀቃል፤ ወይ፡ ቅጣቱ፡ ይቃለልለታል።

በዚህ ርእሰ ነገር ላይ፡ ይህ ኹሉ ሓተታ እንዲቀርብ አስፈላጊ የኾነው፡ እንኳንስ፡ የምሕረትና የርኅራኄ ባለቤትና ምንጭ የኾነው እግዚአብሔር ይቅርና፥ ክፉዎች የኾኑት ሰዎች እንኳ፡ በጥፋተኞች ላይ የቅጣት ፍርድን ለመስጠት ብቻ ሳይኾን፡ ቅጣቱ እንዲቀር፥ ወይም፡ እንዲቃለል ለማድረግ፡ የቱን ያህል ጥረትና ጥንቃቄ እንደሚያደርጉ ለማሳየት ነው።

ክፉዎች በኾኑት፡ በሰዎች ዘንድ እንዲህ የሚደረግ ከኾነ፡ በእግዚአብሔር ዘንድማ፡ ኀዘኔታውና ርኅራኄው፥ ይቅር ባይነቱና መሓሪነቱ፥ ትዕግሥቱና ፍቅሩ፡ የቱን የሚያኽል ሊኾን ነው!? የትየለሌ! "ይህን ያኽላል!" ብሎ፡ መናገሩ ቀርቶ፡ ማሰቡ እንኳ ይቻላልን? ፈጽሞ አይቻልም።

ያ፡ ቸሩ አምላክ፡ ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ "ባልንጀራዬ፡ በቀን ሰባት ጊዜ ቢበድለኝ፡ ሰባቱንም ጊዜ፡ ይቅር ልበለውን?" ብሎ፡ ሓዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ላቀረበለት ጥያቄ፡ "አይ! የለም! የተፈጥሮ ወገንህ፡ በቀን ሰባት ጊዜ ብቻ ሳይኾን፡ ሰባ ጊዜ ሰባት ጊዜም ቢበድልህ እንኳ፡ ይቅር በለው!" ያለው፡ እነዚህን፡ ሳያውቁ በስሕተት የበደሉትን ደካሞቹን ሳይኾን፡ እነዚያን፡ አውቀው በድፍረት የበደሉትን መኾኑን እንዳንዘነጋው ያስፈልጋል።

ስለዚህ፡ የዚህ ሓተታ መካተቻ የኾነው፡ ይህ፡ የመለኮታዊው መምህራችን ቃል አንተ፡ የጥያቄህ፡ ዋና ባለቤቶች ያደረግሃቸውን ኹሉ፡ እንደሚያጠቃልል፡ በማስተዋል ተመልከተው።

ኪዳናዊ ወንድሜ ሆይ!

ላቀረብሃቸው ጥያቄዎችህ፡ ተገቢ መስለው የታዩኝን መልሶች በመስጠት ረገድ፡ ይህን ያህል ካልሁ፡ አኹን ደግሞ፡ ለአንተ ባለኝ፡ ኪዳናዊ ወንድምነቴና ክህነታዊ ባልደረብነቴ፡ ለዚህ ጽሑፍ ማብራሪያዬ፡ ማጠቃለያ የኾኑ፥ ከተነሣንበት ርእስም ጋር፡ "አግባብነት አላቸው!" ያልኋቸውን፡ አንዳንድ ቍም ነገሮችን፡ ከዚህ፡ እንደሚከተለው፡ በተጨማሪ ላበረክትህ እወድዳለሁ።

፩ደኛ. "ንስሓ" የሚለው፡ የሥርዓታችን አንዱ ዓቢይ ዓምድ የኾነው ቃል፡ በዚህ የጥያቄና የማብራሪያ ልውውጣችን ውስጥ፡ ያለው፡ የወሳኝነት ድርሻ፡ የቱን ያህል ከፍተኛ መኾኑን፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የተዋሕዶ ሃይማኖታችንና የቅዱሱ ኪዳናችን፥ እንዲሁም፡ ለሰማዩ አባታችንና ለሰማይዋ እናታችን በምናቀርባቸው የምስጋናና የሰላምታ ጸሎታት ላይ፡ ዘወትር እየተሰማ ያለው መልእክት ያረጋግጣል። እርሱም፡ እንዲህ የሚለው ነው፡-

በቅድሚያ፡ በሃይማኖታችን ጸሎት ውስጥ፡ "ወነአምን፡ በአሓቲ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ይእቲ ዘመሠረታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እምጥንት፥ በኪዳነ ልቦና፡ ዘሰብኣውያን ቀደምት፤ ወዘአጽንዓት፡ በቃለ ነቢያት፤ ወዘፈጸማ፡ በላዕለ ኵሉ ጉባኤ፡ ዘሓዋርያት። በውስቴታ፡ ያቄርቡ ካህናት፡ መሥዋዕተ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ። ወባቲ ይትዌከፉ ምእመናን፥ ወምእመናት፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፡ ዘዘዚአሁ።"

"ወነአምን፡ በአሓቲ ጥምቀት፡ ለሥርየተ ኃጢኣት።"

ማለትም፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጥንት፡ በቀደሙት ሰዎች ኪዳነ ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሐዋርያት ጉባኤ በፈጸማት፥ ካህናት፡ የእርሱን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚያቀርቡባት፥ ምእመናንና ምእመናትም፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋዎች በሚቀበሉባት፡ በአንዲት ቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እናምናለን።"

"ኃጢአት በሚሠረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።" የሚለው አንቀጽ ነው።

በዚህ፡ በሃይማኖቱ ጸሎት ውስጥ፡ "ጸጋ መንፈስ ቅዱስ"፥ ማለትም፡ "የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች" ከተባሉት መካከል፡ "ንስሓ፡" አንዱ መኾኑን ያስተውሷል።

ቀጥሎ፡ በቅዱሱ ኪዳን ጸሎታችን ውስጥ፡ "ነአምን፡ ከመ ብነ ይደልወነ፡ ንሄሉ በንስሓ፡ እንበለ ፅርዓት፡ ለሥርየተ ኃጢአት፥ ወበተመጥዎተ ሥጋሁ፥ ወደሙ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለአጽንዖተ ዝንቱ ወልድናነ፥ ወለትውክልተ ውርስናነ ዘመንግሥቱ፥ ወለዝልፈተ ተልእኮትነ ንጹሕ።"

ማለትም፡ "ይህን ልጅነታችንን፡ አጽንተን ለመጠበቅ፥ የመንግሥቱ ወራሽነታችንን ለማረጋገጥና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፡ ኃጢአታችንን፡ ዘወትር፡ በንስሓ እያጠራንና የክርስቶስን ሥጋና ደም እየተቀበልን መኖር እንዳለብን እናምናለን።" የሚለው አንቀጽ፣

ከዚህ በማስከተል፡ ለሰማዩ አባታችን በምናቀርበው የምስጋና ጸሎታችን ውስጥ፡ "ወመጠከነ በኵሉ ጊዜ፡ ሥጋ ወልድከ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ዘኮነ ለነ፡ ምግበ ነፍስ፥ ወመድኃኒት፡ ዘይረስየነ ሕያዋን ዘለዓለም፤ ወበውእቱሰ፡ ደምሰስከ፥ ወኃደግከ ለነ፡ ኵሎ ኃጢአተነ፥ ወአበሳነ ግሙራ፣ ወዘኢ.ማእዜ፤ ወከማሁ አባሕከነ፡ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ኵሎ፡ ለዘአበሰ ለነ።

"ወአልዓልከነ፡ በልደተ መንፈስ ቅዱስ ዘጥምቀት፡ በዘውእቱ በጻሕነ፡ ከመ ንኩን ውሉድከ፥ ወአዋልድከ፤ ወበጸጋከ ዘንስሓ።"

ማለትም፡ "ለዘለዓለም፡ ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንንም፡ የልጅህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን። በእርሱም፡ ኃጢአታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ፡ ደምስሰህ፡ ፈጽመህ ይቅር አልኸን። እኛም፡ የበደሉንን ኹሉ፡ ይቅር እንድንል አስቻልኸን።

"የአንተ ልጆች ለመኾን የበቃንበትን፡ የጥምቀትን ልደትና የንስሓን ጸጋ አደልኸን።" የሚለው አንቀጽ፣

እንዲሁም፡ ለሰማይዋ እናታችን በምናቀርበው፡ የሰላምታ ጸሎታችን ውስጥ፡ "ንዌድሰኪ ወትረ፡ እንዘ ንብል፡ "ብፅዕት አንቲ፡ አ ምልዕተ ጸጋ!" እስመ ዐተበ እግዚአብሔር፡ ኪዳኖ ዘምሕረት፡ ለዓለመ ዓለም፡ በዘአጥረየኪ አንቲ፡ ለምክንያተ ድኅነትነ።"

ማለትም፡ "እግዚአብሔር፡ አንቺን፡ የድኅነታችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳነ ምሕረቱን፡ ለዘለዓለም ፈጽሟልና፡ 'ጸጋን የተመላሽ፡ ብፅዕት ነሽ!' እያልን፡ ዘወትር እናወድስሻለን።" የሚለው አንቀጽ፡ በኪዳናዊው ሕይወታችን ውስጥ፡ "ንስሓ" ምን ዓይነቱን ከፍተኛ ሥፍራ ይዞ እንደሚገኝ፡ በሚበቃ ያስረዳል።

የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ መሠረታዊና ቀዳማዊ ተልእኮዋ፡ አዎን! ሰዎችን፡ ወንዶችንም፥ ሴቶችንም፡ ለንስሓ ሕይወት ማብቃት መኾኑን፡ ለአንተ፤ ለኪናዊው ኢትዮጵያዊ መናገር አያስፈልግም።

እንዲህ ከኾነ፡ እነዚህ፡ ንስሓ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች ደግሞ፡ አንተ፡ ኪዳናዊው ወንድሜ፡ በጥያቄህ ውስጥ አካትተህ ያቀረብሃቸው፡ ከሃዲዎቹና ዓመፀኞቹ፥ አመንዝሮቹና ክፉዎቹ፥ ርኵሶቹና ርጉማኑ ስለኾኑ፡ እኛ፡ ኪዳናውያኑና ኪዳናውያቱ የእግዚአብሔርና የቅድስት እናቱ የኢትዮጵያ ልጆችና አገልጋዮች፡ እነዚህን ኃጢኣተኞች፡ ለንስሓ በማብቃት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው የኢትዮጵያ ልጆችና ዜጎች፥ ካህናትና ነጋሢዎች እንዲኾኑ ለማድረግ፡ በዚህ ረገድ፡ የሚጠበቅብንን ተልእኮ እያካኼድን መቀጠል ይኖርብናል ማለት ነው።

ስለንስሓ፡ ያለንን ሃይማኖታዊ አቋም፡ ባጭሩ ለመጥቀስ ያህል፡ ይህን ካልሁ፡ አኹን ደግሞ፡ "ንስሓ" ምን ማለት እንደኾነ፡ እስኪ፡ በበለጠ ላብራራ!

"ንስሓ"፡ በአግባቡና በትክክል አልተሠራበትም እንጂ፡ ራስን፡ ከኃጢኣት፡ ወደጽድቅ፤ ማለትም፡ ከሓሰት፡ ወደእውነት፥ ከክፋት፡ ወደደግነት፥ ከምውትነት፡ ወደሕያውነት፡ በፍጹም ታማኝነት መመለስ እንደኾነ፡ በዘልማድ ሲነገር የተኖረ መኾኑ፡ በኹሉ ዘንድ ይታወቃል።

እዚህ ላይ ግን፡ "ንስሓ" ስንል፡ እውነተኛውን ዓይነት ማለታችን እንጂ፡ "ጾም ገድፌአለሁ! አራስ ጠይቄ፡ ጠበል ሳልረጭ፥ ቤተ ክርስቲያን ገብቻለሁ! በሴትነቴ፡ በቤተ ልሔም በኩል አልፌአለሁ! ካደፌ ሳልጠራም፡ ጠበል ጠጥቻለሁ! በበዓልና በጾም ወራት፡ ከባለቤቴ ጋር፡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት አድርጌአለሁ! በበዓል አርሻለሁ! ወፍጮ ፈጭቻለሁ! በሕማማት፡ ልብስ አጥቤአለሁ! ቅማል ገድዬአለሁ!" የሚለውንና ይህን የመሰለውን፥ በታላቁ የንስሓ ጸጋ ላይ፡ እንደመሣለቅ የሚያስቈጥረውን፥ ኃጢኣት ያልኾነውን፡ ጥቃቅንና የማይረባውን፡ ሰው ሠራሽ ወግ ተከትሎ የሚፈጸመውን አይደለም፡ እኛ፡ ንስሓ የምንለው።

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ ያለው፡ የንስሓ፡ ትክክለኛ ትርጉሙ፥ ተገቢ አፈጻጸሙም፡ እንዲህ ነው፡-

ከላይ የተገለጸው ይትበሃል፡ እንዳለና እንደተጠበቀ ኾኖ፡ "ንስሓ"፡ ማለት፡ ሕያውቷ ነፍስ፡ ገና፡ ለወጣኒነት ማዕርግ እንኳ ካልበቃውና ዝቅተኛ ከኾነው፡ ሥጋዊ አካሏና ባሕርይዋ፡ ራሷን፡ ነጻ አውጥታና ከፍ አድርጋ፡ እርሱን፡ ሥጋን ጭምር፡ ለመቆጣጠርና ለመምራት፡ ባላት መንፈስ ቅዱሳዊ ሥልጣንና ኃይሏ ተጠቅማ፡ ከፍጹምነት ማዕርግ ሊደርስ ለሚችለውና ሉዓላዊ ለኾነው፡ ለመንፈሳዊው አካሏና ባሕርይዋ፡ ያንኑ ራሷን ማብቃት ነው።

ምክንያቱም፡ እንዲያ ካልኾነ፡ ማለትም፡ ነባቢቷ፥ ለባዊቷና ሕያውቷ ነፍስ፡ ራሷን ብቻ ሳይኾን፡ ሥጋዊ አካሏንና ባሕርይዋን ጭምር ይዛ፡ ጥንቱኑ፡ "በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረች!" በፍጻሜ ዘመንም፡ በድንግል ማርያም በተከሠቱት ቅድስት ሥላሴ፡ "ከእኛ፡ እንዳንዱ ኾነች!" ለተባለችበት መንፈሳዊው አካሏና ባሕርይዋ፡ ራሷን አብቅታ ካልተገኘች በቀር፡ በራሱ፡ በሥጋ ብቻ፡ የንስሓን ምሥጢር አውቃ፡ አማናዊዉን [እውነኛውን] ንስሓ በመፈጸም፡ የጸጋው ተሳታፊ ለመኾን፡ ከቶ አይቻላትም። ሥጋ ብቻውን፡ መንፈሳዊ የኾነውን፡ የንስሓን ምሥጢራዊ ምንነትና ዝክረ ነገር ለማወቅና ለመረዳት፡ ፈጽሞ ዓቅሙ የለውም። ሓዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡ "ወሰብእሰ ዘነፍስ፡ ኢይኤድሞ ዘመንፈስ፤ ወኢይትዌከፎ፤ እስመ ዕበደ ይመስሎ፤ ወኢይክል ያእምር፡ ከመ በመንፈስ ቅዱስ ይትሓተት።

ማለትም፡ "ለሥጋዊ ሰው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር፡ ሞኝነት ስለሚመስለው፡ አይፈልገውም፤ አይቀበለውምም። በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ተመርምሮ የሚታወቅ ስለኾነ፡ በሥጋዊ አእምሮው ሊያውቀውና ሊደርስበት አይቻለውም። ያለውም፡ ለዚህ ነው። (፩ኛ ቆሮ. ፪፥ ፲፬-፲፮።)

ደግሞም፡ ማንም ሰው፡ ሰብአዊ ነፍሱ፡ በመንፈሳዊ አካሏና ባሕርይዋ አእምሮ ካልኾነ በቀር፡ በሥጋዊው አካሏና ባሕርይዋ አእምሮ፡ እግዚአብሔር አብንና እግዚአብሔር "እም"ን፡ እርሷም፡ ድንግል ማርያምን፥ እግዚአብሔር ወልድንና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ለማወቅ እንደማይቻላት ሊያስረዳን፡ ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ የፊልጶስ አገር ወደምትኾን፡ ወደቂሣርያ ከተማ እንደደረሰ፡ ያደረገውንና የተናገረውን ተመልከተው፡-

ሰዎች፡ እርሱን፡ የማርያምን ልጅ፡ ማን እንደሚሉት፡ ደቀ መዛሙርቱን በጠየቃቸው ጊዜ፡ ስምዖን ጴጥሮስ፡ "አንተ ውእቱ፡ ክርስቶስ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው!"

ማለትም፡ "አንተ፡ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!" ብሎ፡ ሃይማኖታዊዉን የብቅዓት መልስ ስለሰጠው፡

ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ "ብፁዕ አንተ፡ ስምዖን ወልደ ዮና! እስመ ኢከሠተ ለከ፡ ዘሥጋ ወደም፤ አላ አቡየ ዘበሰማያት።"

ማለትም፡ "አንተ! የዮና ልጅ ስምዖን! ይህን እውነት የገለጠልህ፡ የሰማዩ አባቴ እንጂ፡ ሥጋዊዉና ደማዊው አእምሮህ አይደለምና፡ ብፁዕ ነህ!" ብሎ ምሥጢሩን እንደገለጠለት እናውቃለን።

እዚህ ላይ፡ ይህ፡ የእግዚአብሔር እውነታ፡ ለቅዱስ ጴጥሮስ፡ እንዴት ሊገለጥለት እንደቻለ፡ አስተውሎ መመልከቱ፡ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ፥ ተገቢም ኾኖ ይገኛል። ምክንያቱም፡ ያ፡ ያለማመን ችግር፡ ዛሬም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ! ዐማራ ነኝ! ክርስቲያን ነኝ!" በሚለው ዘንድ ሳይቀር፡ ጎልቶ ስለሚታይ፥ ገዝፎም ስለሚገኝ፡ ይህን እውነታ ማወቁ፡ ያን ችግር ለማስወገድ እንደሚረዳ የታመነበት ስለኾነ ነው።

አዎን! ጌታችን፡ "አቡየ ዘበሰማያት፥ የሰማዩ አባቴ" ያለው፡ እግዚአብሔር አብ፡ በእያንዳንዳችን እንዳደረገው ኹሉ፡ በቅዱስ ጴጥሮስም ሰውነት ውስጥ፡ ጥንቱኑ፡ ከኹለቱ አካላቱና ባሕርያቱ ጋር፡ ማለትም፡ ከነፍሱና ከሥጋው ጋር፡ ሦስተኛ አካልና ባሕርይ አድርጎ፡ በተፈጥሮና በተዋሕዶ ያስገኘው፡ የቅዱስ ጴጥሮስ መንፈስ፡ <u>ከመንፈስ ቅዱስ</u> የተከፈለ መኾኑ፡ በአንድ ወገን ሊታወቅ ይገባል።

በሌላው ወገን ደግሞ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ፡ በገዛ ፈቃዱና ፍላጎቱ፡ ራሱን፡ ከሥጋዊው ማንነቱ አውጥቶ፡ ለዚያ መንፈሳዊ ማንነቱ ሊያበቃ፥ ያ፡ እግዚአብሔራዊ እውነታም ሊገለጠለት የተቻለው፡ በዚያ መንፈሳዊ ሥልጣኑና ኃይሉ ለመጠቀም፡ በቊርጠኝነት በመወሰኑ መኾኑን፡ መገንዘቡ፡ አስፈላጊ ይኾናል።

እንደዚሁ ኹሉ፡ አኹንም፡ ሰዎች፡ ሴቶችም ኾኑ ወንዶች፡ ስለንስሓ፡ እውነቱን አውቀው፡ እውነተኛውን ንስሓ ለመፈጸም፡ በቅድሚያ፡ እየራሳቸውን፡ ከሥጋዊው ማንነታቸውና አስተሳሰባቸው አውጥተው፡ ለመንፈሳዊው አካላቸውና ባሕርያቸው ማብቃት ይኖርባቸዋል። አለዚያ፡ ስለንስሓ የሚያውቁትና የሚያስቡት፥ የሚናገሩትና የሚያደርጉት፡ ገና በሥጋዊው አካላቸውና ባሕርያቸው ብቻ ይኾንና፡ በንስሓ ጸጋ መጠቀሙ ቀርቶ፡ ስለንስሓ ምንነት፡ እውነተኛውን ግንዛቤ የማግኘቱ ዕድል እንኳ፡ ከእነርሱ የራቀ ይኾንባቸዋል። (ማቴ. ፲፮፥ ፲፫-፳።)

እስካኹን እንደታየውና አኹንም፡ እየታየ ባለው ኹኔታ መመልከት እንደሚቻለው፡ የሰዎች ንስሓ፡ እውነተኛ ኾኖ፡ በመንፈስ የሚፈጸም ሳይኾን፡ በሥጋ ብቻ የሚቀርብ፡ የሓሰት በመኾኑ፡ እነሆ፡ መከሩ፡ ከበረከት ይልቅ፡ መርገምን፥ ከተድላ ደስታ ይልቅ የኃዘን ለቅሶን፥ ከፍቅር ይልቅ ጠብን፥ ከሰላም ይልቅ ጦርነትን፥ ከብልጽግና ይልቅ ደሀነትን፥ ከዕረፍት ይልቅ መከራን፥ ከሕይወት ይልቅ ሞትን መሰብሰብ እንደኾነ፡ በሚበቃ የተረጋገጠ ኾኗል።

ሓዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡ ይህን እውነታ፡ አኹንም፡ እንዲህ ሲል፡ አሳምሮና ግልጽ አድርጎ፥ አብራርቶታል፦ "**ወኀሊናሁሰ ለነፍስትነ፡ ሞተ ያመጽእ ላዕሌነ፤ ወኀሊናሁሰ ለመንፈስ፡ ሰላመ፥ ወሕይወተ ይሁበነ። እስመ ኀሊናሁ ለነፍስትነ፡ ፀሩ ለእግዚአብሔር ውእቱ። እስመ ኢይገርር ለሕገ እግዚአብሔር፤ ወኢሂ ይክሎ። እስመ ኵሎሙ፡ እለ ለግዕዘ ነፍስቶሙ ይገብሩ፣ ለእግዚአብሔር አድልዎ ኢይክሉ።**"

ማለትም፡ "ነፍሳችን፡ በሥጋዊ አእምሮዋ የምታስበው ኹሉ፡ ሞትን የሚያመጣብን ኾኗል፤ በመንፈሳዊ አእምሮዋ የምታስበው ኹሉ ግን፡ ሰላምንና ሕይወትን አስገኝቶልናል። የነፍሳችን ሥጋዊ አእምሮ አሳብ፡ ምንጊዜም፡ እግዚአብሔርን መቃወም ብቻ ነው፤ ይኸው ሥጋዋ፡ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፤ መገዛትም ተስኖታል። አስተሳሰባቸው፡ በሥጋ ብቻ ኾኖ የሚኖሩ ኹሉ፡ እግዚአብሔርን፡ ደስ ሊያሰኙት አይችሉም።" (ሮሜ ፰፥ ፯-፰።)

፪ተኛ. ሰው፡ በፍጥረተ ዓለሙና ከፍጥረተ ዓለሙ ተገኝቶ፡ በእውቀት ሥርዓት መኖርን ከጀመረበት፡ ከዛሬ ፯ሺ፭፻፯ ዓመታት ወዲህ፡ በአንድ ወገን፡ በአሉታዊው ገጽታውና ዝንባሌው፡ የእግዚአብሔር በኾኑት፡ በእውነት፥ በደግነትና በሕይወት ላይ፡ ክህደትን፥ ዓመፅንና አመንዝራነትንም በመፈጸም፡ በሌላው ወገን ደግሞ፡ የዲያብሎስ ለኾኑት ለክፋት፥ ለሓሰትና ለሞት ግን፡ ታማኝነትን፥ ድጋፍንና ተባባሪነትን በማበርከት ረገድ፡ የቱን ያህል ንቁና ትጉህ፥ ብልህና ኃይለኛ እንደኾነ፥ ይህም ኹኔታ፡ አኹንም፡ በበለጠ እየቀጠለ እንደሚኼድ፡ ይኸው እየታየ ነው።

ይህን ኹኔታ፡ ቢቻል፡ ፈጽሞ በመለወጥ፡ ወደቀደመ ፍጹምነቱ ለመመለስ፥ ካልኾነም፡ ለማሻሻል፥ ካልተቻለም፡ እየባሰ እንዳይኼድ፡ ባለበት ለመግታት፡ በእግዚአብሔር ልጆችና አገልጋዮች የተደረገው ጥረት ሳይሳካ በመቅረቱ፡ በመጨረሻ፡ በተለያየ መልክ በተገለጸው፡ በራሱ፡ በእግዚአብሔር ባለቤትነትና መሪነት፥ አስተማሪነትና ተጋዳይነት፡ የራሱን መሥዋዕትነት በመክፈል ጭምር፡ ፍጥረቱን፡ እነሆ፡ አብቅቶለት ከነበረው፡ የጥፋት ፍጻሜ ለማዳን ተችሎ፡ ይኸው፡ ዛሬ፡ እኛ ካለንበት ዘመንና ኹኔታ ላይ ደርሰን፡ እየኖርን እንገኛለን።

ኪዳናዊ ወንድሜ ሆይ!

ዛሬ፡ በዘመንህ ያለውና በራስህ የምታውቀው፡ ይኸው ሰው፡ ራሱ እግዚአብሔር ሰው ኾኖ፡ እውነቱን እያሳየውና እያስተማረው፡ ጉልህና ተጨባጭ ማስረጃንም እየሰጠው ሊያሳውቀው የሞከረውን፤ ነገር ግን፡ በመጨረሻ፡ "በሰውነት ተፈጥሮዬ የገለጽህልኝን፡ የአንተን እውቀት፥ እንዲሁም፡ በተአምራትህ እያሳየህና እያረጋገጥህ፡ ያስተማርኸኝንም፡ የአንተ የኾነውን ትምህርት፥ እንቢ! አልቀበልም! አልፈልግም!" ብሎ፥ እንዲያውም፡ እንዲህ፡ በጎ ያደረገለትን፡ ያን፡ ሰው የኾነ አምላክ፡ በመስቀል ላይ አሠቃይቶ እንደገደለው ታውቃለህ።

ታዲያ! እንዲህ ያለው፡ ያው ሰው፡ ዛሬ፡ ከአንተ፥ ወይም፡ ከእኔ ተምሮና አውቆ፡ ይኸው አኹን፡ አንተ፡ በጥያቄ መልክ፡ ዘርዝረህ ያቀረብሃቸውን፤ እነዚያን ትእዛዛትና ሕግጋት፥ ቀኖናትና ሥርዓታት ሰምቶና ተረድቶ፥ ተቀብሎና አምኖባቸው፡ ሊፈጽማቸው ይችላል ብለህ፡ እንዴት አሰብኸው?

ለመኾኑ፡ ለሰው፡ ከእግዚአብሔር የተሻለና የበለጠ አስተማሪ አለውን? ሊኖረውስ ይችላልን? እግዚአብሔርስ፡ እያንዳንዱን ሰው፡ ጥንቱኑ፡ በራሱ መልክ በመፍጠሩ፥ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" በሚለው ቃሉም መሠረት፡ ለሰው፡ በተፈጥሮ በሰጠው፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ አካላትና ባሕርያት፥ ከዚያም ጋር፡ ከአካባቢው በማይለዩትና ዐብረውት በሚኖሩት፡ በሥነ ፍጥረትና በታላላቆቹ የእውነት ሰዎቹ አማካይነት፡ ቀድሞ፡ ለአምስት ሽህ አምስት መቶ ዓመታት፥ ኋላስ፡ በሰውነት፥ በመጨረሻስ፡ በመንፈስ፡ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፡ ራሱ አላስተማረውምን? ኹሉንስ አላሳወቀውምን? አዎን! አስተምሮታል፤ አሳውቆታል።

ከዚህ በላይ ማሳወቅ፥ ከዚህ የበለጠ ማስተማር አለን? የለም፤ ሊኖርስ ይችላልን? አይችልም። እግዚአብሔር፡ እንዲያ በሰውነት፡ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፡ በሰዎች መካከል እየተመላለሰ በነበረበት፡ በዚያን ጊዜ፡ አይሁድ፡ "እፎ የአምር ዝንቱ፡ መጽሐፈ፡ ዘኢመሃሮ መኑሂ!?"

ማለትም፡ "ይህ ሰው፡ ማንም ሳያስተምረው፡ እንዴት፡ መጻሕፍትን ሊያውቅ ቻለ!?" ብለው ሲደነቁ ሣለ፡ የሰጣቸው መልስ፡ "ትምህርትየሰ፡ ኢኮነት እንቲአየ፤ አላ እንቲአሁ፡ ለዘፈነወኒ። ወዘሰ፡ ይፈቅድ ይግበር ሥምረቶ፡ ውእቱ የአምር፡ ከመ እምኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ትምህርትየ፤ ወአኮ ዘእምኀቤየ፡ ዘእነግር"

ማለትም፡ "ትምህርቴስ፡ የእኔ አይደለም፤ የላከኝ፡ የእርሱ እንጂ። የእርሱንም ፈቃድ ሊደርግ የሚወድድ ቢኖር፡ ትምህርቴ፡ ከእግዚአብሔር እንጂ፡ እኔ፡ ከራሴ የምናገረው እንዳይደለ፡ ያ ሰው ያውቃል።" የሚል እንደነበረ ይታወሳል።

መለኮታዊው መምህራችን ኢየሱስ መሢሕ፡ ይህን እውነታ በሚመለከት፡ እንዲህ ብሎ የተናገረው፡ ስለራሱ ብቻ ሳይኾን፡ ስለእኛ፡ ስለሰዎችም ጭምር መኾኑን፡ ከዚሁ ጋር የተያያዙ፡ አንዳንድ ቃላቱን፡ አክለን ልንጠቅሳቸው ይቻለናል፤ እነሆም፡ እንዲህ የሚሉት ናቸው፡-

አይሁድ፡ እርሱን፡ "አኮኑ፡ ዝንቱ ውእቱ ኢየሱስ ወልደ ዮሴፍ፡ ዘለሊነ ነአምር፡ አባሁ ወእሞ? ወእፎ እንከ ይብለነ እምሰማይ ወረድኩ!?"

ማለትም፡ "ይህ ሰው፡ እኛ እየራሳችን፡ አባቱንና እናቱን የምናውቃቸው፡ የዮሴፍ ልጅ፡ ኢየሱስ አይደለምን? ታዲያ! እንዴት፡ 'ከሰማይ ወረድሁ!' ይለናል?" ብለው፡ ባንጐራጐሩ ጊዜ፡ የሰጣቸው መልስ፡ "ኢታንጐርጕሩ በበይናቲክሙ! አልቦ ዘይክል መጺአ ኀቤየ፡ እመ ኢሰሐቦ አብ፡ ዘፈነወኒ። ...ወሀሎ ጽሑፍ፡ ውስተ መጽሐፈ ነቢያት፡ ከመ ይከውኑ ኵሎሙ፡ ምሁራነ፡ እምኀበ እግዚአብሔር፤ ወኵሉ እንከ፡ ዘሰምዐ በኀበ አቡየ፡ ተምሂሮ፡ ይመጽእ ኀቤየ።"

ማለትም፡ "እርስ በርሳችሁ አታንጐርጕሩ! የላከኝ እግዚአብሔር አብ፡ ወደእርሱ ያቀረበው ካልኾነ በቀር፡ ወደእኔ ሊመጣ የሚችል የለም። ኹሉም፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ እንደሚኾኑ፡ በነቢያት መጽሐፍ፡ የተጻፈ ቃል አለ፤ እንግዴህ፡ ከአባቴ የተገለጸለትን የሰማ፥ የተማረም፡ ወደእኔ ይመጣል።" (ዮሐ. ፯፥ ፴፩-፴፫። ፯፥ ፲፰-፲፯።)

እንግዴህ፡ የሰው ያልኾነው፡ የእግዚአብሔር አስተማሪነት ይህ ነው። ከዚህ የተነሣ፡ እያንዳንዱ ሰው፡ ሴት ኾነች ወንድ፥ ከፈጣሪው፡ በተፈጥሮው በተሰጠው ፍጹም ሥልጣንና ኃይል፡ እንደቅዱስ ጴጥሮስ፡ በእየራሱ፡ የግል ምርጫና ውሳኔ ተጠቅሞ፡ የእግዚአብሔርን አስተማሪነት፡ በእየራሱ ተማሪነትና ተቀባይነት፥ ፈቃደኛነትና አማኝነት፡ እውን አድርጎ፡ በተግባር ላይ ሊያውለው እንደሚቻለው፡ ከላይ በተጠቀሱት አብነቶችና ተመሳሳይ ኹኔታዎች፡ በሚበቃ ታውቋል።

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ ሰብአዊው ፍጡር፡ "እኔ፡ አዋቂና የተማርሁ፥ ከሌላውም ሰው ይልቅ የተሻልሁ፡ ብልህና ብልጥ ነኝ!" የሚል ስለኾነ፡ የእግዚአብሔርን እውነትና እውቀት፡ እንዲህ፡ በእየራሱ ካልኾነ በቀር፡ የሌላ ፍጡርን ቀርቶ፡ የፈጣሪውን አስተማሪነት እንኳ፡ ሊቀበል እንዳልቻለ፡ በፍጹም እርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ይኸውም፡ በተለይ፡ በኢየሱስ መሢሕ በኩል የኾነውንና የተፈጸመውን፥ በእርሱም ላይ የደረሰውን ኹሉ፡ አብነት በማድረግ ነው።

ይኸው ሰብኣዊ ፍጡር፡ ከፈጣሪው ባገኘው፡ የምንነቱና የማንነቱ ታላቅ ጸጋ ምክንያት፡ ከፈለገና በፈለገ ጊዜ፥ የፈለገውንም ዓይነት እውቀትና ትምህርት፡ በራሱ ለመማርና ለማስተማር፥ ለማወቅና ለማሳወቅ፥ ለመረዳትና ለማስረዳት ይቻለዋል። ካልፈለገም ደግሞ፡ እንዲሁ ነው፤ አይቻለውም። በዚህ ረገድ፡ ለዚያ ሰብኣዊ ፍጡር፡ ከራሱ ያለፈ፡ የሌላ ፍጡር እርዳታ እና/ወይም ድጋፍ፡ ከቶ አያስፈልገውም።

እኛም ዛሬ፡ እንደመምህራችን መሢሕ ኢየሱስ፡ ሰዎች በጻፏቸው "ቅዱሳት" በተባሉት መጻሕፍት ውስጥ የተመዘገቡትን፡ "የእግዚአብሔር ናቸው" የተባሉትን፡ ቃላት፡ "እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል!" እያልን ብንጠቃቅስ፡ ምን ረብኅን፥ ምን ጥቅምን አስገኘ? አላስገኘም። እንደቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት እምነትም፡ እግዚአብሔር በየልባችን ጽላት ላይ የጻፋቸውን የእግዚአብሔር ቃላት፡ ከአንደበታችን እያወጣን፡ በድምፅ ብናሰማስ፡ ከጥቂቶች በቀር፡ ማን ሰማን? የሰማን የለም።

ስለዚህ ነው፡ እያንዳንዱ ሰው፡ በውስጡ የሚገኘውንና የራሱ የኾነውን፥ እንደሥጋ አካልና ባሕርይ፡ ከእግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ፡ ለነባቢት ነፍሱ የተሰጠውን፥ በልማድ፡ "ኅሊና" የሚባለውን፡ መንፈሱን፡ የማይሰማ ከኾነ፡ ማንም ፍጡር ቢነግረው፡ ሊሰማና የሰማውን ሊቀበል የማይቻለው። ይህም እውነታ፡ ያው፡ በመሢሑ ኢየሱስ የመምህርነት ዘመን በነበሩት አይሁድ ላይ፡ በገሃድና በግዘፍ ተገልጾ ታይቷል።

ሰው ኹሉ፡ እንኳንስ ከተፈጥሮ መሰሉ ቀርቶ፡ ከፈጣሪውም ቢኾን፡ ሊማር፥ በእውነት ሊሰማና፡ በንስሓ ሊመለስ የሚችለው፡ ፍጹም መልካም በኾነ፡ በአንድ ረቂቅ ኃይል ብቻ መኾኑን፡ ኹሉን ከሃሊ የኾነው አምላክ፡ በመለኮትነቱ አወቀ። ያም ኃይል፡ ፍቅር ኾኖ ተገኘ። ስለዚህ፡ ያ ሰው፡ በትምህርቱና በእውቀቱ ረገድ ጭምር፡ የእግዚአብሔር የኾነውን ኹሉ፥ ልቡናው ተነክቶና ተሰምቶት፡ በራሱ ፍላጎትና ፈቃድ እንዲቀበለው ለማድረግ፡ እርሱ፡ ራሱ እግዚአብሔር፡ ቃልም፥ ሰውም፥ መንፈስም ኾኖ፡ በበረት ውስጥ በተወለደበት ሰውነቱና በመስቀል ላይ በተሠዋበት ቤዛነት፡ ወደር የሌለውን ፍጹም ፍቅሩን፡ ለዚሁ ፍጡሩ አሳየው።

አዎን! በገዛ ራሱ ፈቃድና ምርጫ፡ ራሱን አጥፍቶ የነበረው፥ በመጨረሻም፡ በፈጣሪው ፍለጋ የተገኘው፡ ይኸው ሰብኣዊ ፍጡር፡ የእግዚአብሔር የኾነውን ኹሉ፡ ትምህርቱንና እውቀቱን ጭምር ሊቀበል የሚችለው፡ እንዲህ፡ በመለኮታዊው ፍቅር እንጂ፡ በማንም አስተማሪ፥ ወይም፡ በማንኛውም ዓይነት ትምህርት አለመኾኑን፡ የቅዱሱ ኪዳን አምላካችን፡ በመለኮትነቱ ተረዳ።

በዚህ ጊዜ፡ ከተቃዋሚው፡ ከዲያብሎስ ጋር ዐባሪ ተባባሪ ኾኖ የተገኘውን፡ ይህንኑ ፍጡሩን ያሸነፈውና ወደእርሱ ዕቅፍ መልሶ ያስገባው፡ በፍቅሩ መኾኑን፡ እኛም፡ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን ሳንቀር፡ በእየራሳችን ሕይወት፡ እነሆ፡ ለመገንዘብ ቻልን። ስለዚህ፡ ይህንኑ እውነታ አጽንተን፡ እኛም፡ የእርሱን፡ የቸሩ ፈጣሪያችንን ፈለግ በመከተል፡ ተልእኳችንን፡ በዚሁ መልክና ይዘት፡ ልንፈጽም እንደሚገባን ላሳስብ እወድዳለሁ።

ለነገሩ፡ ለሰው፡ ቀላሉና ተፈጥሮአዊው፥ እውኑም ቊም ነገር፡ እግዚአብሔርን መምሰሉ፡ ማለትም፡ ደግ፥ እውነተኛና ሕያው መኾኑ፡ እንጂ፡ የዚህ ተቃራኒው፡ እንዲህ፡ ሰይጣንን መምሰሉ፡ ማለትም፡ ክፉ፥ ሐሰተኛና ሟች መኾኑ አልነበረም። ነገር ግን፡ የሰው ፍላጎትና ምርጫ፥ በሰው ዘንድ እየታየ ያለውም፡ ይህ፡ አኹን፡ አንተ፡ "እየኾነ ያለ ነው!" የምትለው ኹኔታ በመኾኑ፡ "**እፎ ዕፁብ በዊእ፡ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር!?**"

ማለትም፡ "**ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት፡ እንዴት ጭንቅ ነው!?**" ያሰኘው፡ እንግዴህ፡ ይህ ነው። (ሉቃ. ፲፰፥ ፳፬።)

"ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት" ማለት ደግሞ፡ "እግዚአብሔርን መምሰል" ማለት ነው፤ እግዚአብሔርን ካልመሰሉ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት የለምና። ስለዚህ፡ ለሥጋውያንና ለሥጋውያት፥ ለዓለማውያትና ለዓለማውያን፡ "እግዚአብሔርን መምሰል"፡ ጭንቅ እንደሚኾን ይታወቃል።

የሌለውን ችግር፡ ራሱ ፈጥሮና ያን ችግር በራሱ ላይ አምጥቶ፣ በዚያ ችግር፡ መልሶ ራሱ የሚሠቃየውንና ለችግሩ ማስወገጃ የተሰጠውን ፍቱን መድኃኒትም፡ "እንቢ!" አልቀበልም!" ያለውን፥ እንዲህ አስቸጋሪ የኾነውን፡ ሰብአዊ ፍጡሩን ነው፡ እንግዴህ፡ ቸሩ ፈጣሪ፡ ፈልጎ ያገኘውና ያዳነው። ካገኘውና ካዳነውም በኋላ፥ ወደቀደመ ክብሩ የመለሰው። ከመለሰውም በኋላ፡ አኹንም፡ ይኸው ፍጡሩ፡ በዚያው ጥፋቱ መቀጠሉን አይቶና አውቆ፡ በእርሱ፡ በፈጣሪነቱ በኩል፡ ማስተማሩና መገሠፁ፥ በፍጡሩ ሰውም በኩል፡ መማሩና ተግሣፅ መቀበሉ፡ እስካኹን፡ ግልጽ ኾኖ በሚታየው ኹኔታ እንደተረጋገጠው፡ ምንም ዓይነት ረብኅ ጥቅም እንደሌለው፡ ፈጣሪ፡ ለራሱ አውቆ፡ ለፍጥረቱም የከሠተው።

የእግዚአብሔርን እውነት፡ ለሰው፡ በማሳወቁና በማስተማሩ ረገድ የተደረገው ይህ ኹሉ ታላቅ ገድል፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እንደማይሠምርና እንደማይጠቅም፥ እንደማይኾንም፡ ቸሩ ፈጣሪ፡ በአምላክነቱ ስለተረዳው፡ ቅድስት ሥላሴነቱ በተገለጠባትና ለእግዚአብሔርነቱ እናትነት በበቃችው፡ በድንግል ማርያም መለኮታዊና ሕያው ሰውነት፡ ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ቃል ኪዳን ሓውልቱን አቆመ። አዎን! በእግዚአብሔራዊው አባትነቱና እናትነቱ፥ ልጅነቱና መንፈስነቱ ያቆመውን፡ ይህንኑ ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ቃል ኪዳን፡ ዐትሞና ዐውጆ ፈጸመው።

# ምሥራቹ!

በዚህ ዐዋጅ፡ አንድ ታላቅ ምሥራች ተናገረ። ይህን የምሥራች ቃል፡ ኪዳናዊ ወንድሜ ሆይ! አንተም፥ እኔም፡ እንኪ እንስማው!

"በቃ እንግዴህ! ሰብአዊው ፍጡራችን፡ ስለደኅንነቱም፥ ስለጥፋቱም፡ እንደፈለገውና እንደመረጠው ይኹን! እኔ ግን፡ ለአንዴና ለዘለዓለም ምሬዋለሁ!"

ይህ፡ አጭር የዐዋጅ ቃል፡ መሢሕ ኢየሱስ፡ የቅርብ ደቀ መዝሙሩ ለኾነው፡ ለዮሓንስ፡ በራእዩ ተገልጾ ከተናገረው፡ እንዲህ ከሚለው መመሪያው ጋር ይስማማል፦ "**ወኢትኅትም ቃለ ተነብዮቱ ለዝንቱ መጽሓፍ፤ እስመ በጽሐ ዘመኑ። ወለዘገፍዐኒ፡ ይገፍዕዎ እንከ፤ ወለዘረስሐኒ፡ ያረስሕዎ እንከ፤ ወጻድቅ፡ ለይጽደቅ፤ ወንጹሕኒ፡ ለይንጻሕ። ወናሁ፡ እመጽእ ፍጡነ፤ ወዕሤትየኒ፡ ምስሌየ ውእቱ፤ ከመ እፍድዮ፡ ለለአሐዱ፤ ወእኩንኖ፡ በከመ ምግባሩ።**"

ማለትም፡ "**የዚህን መጽሓፍ፡ የትንቢት ቃል፡ አትዝጋው! ዓመፀኛው፡ በዓመፁ ይቀጥል! ርኵሱም፡ በርኵሰቱ ይቀጥል! እውነተኛውም፡ በእውነተኛነቱ ይቀጥል! ንጹሑም፡ በንጽሕናው ይቀጥል! እነሆ፡ ፈጥኜ እመጣለሁ። ለእያንዳንዱ፡ እንደየሥራው መጠን፡ ፈርጄ፡ እከፍለው ዘንድ፡ ዋጋዬ፡ ከእኔ ጋር አለ።**" (ራእ. ፳፪፥ ፲-፲፩።)

እንዲህ፡ የቸርነትና የምሕረት ጸጋው ተትረፍርፎ የፈሰሰ መኾኑን የሚያረጋግጠውን፡ ያን ከላይ የሠፈረውን፡ አምላካዊ ዐዋጅ፡ የሚያብራሩና የሚያጸኑ፡ መሢሕ መምህራችን ኢየሱስ፡ ለቀደሙትና ለእኛ ለአገልጋዮቹ ከተወልን መመሪያ ቃላት መካከል፡ ጥቂቶቹን፡ ከዚህ እንደሚከተለው እጠቃቅሳቸዋለሁ፤ የምጠቃቅሳቸውም፡ በሰማዩ አባታችንና በሰማይዋ እናታችን አንደበት ይኾናል፦

፩. "በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በመልካችንና እንደአንዳችን አድርገን የፈጠርናችሁ፥ በሕያውነትም የምናኖራችሁ፡ እኛ፡ ለእናንተ፡ የዘለዓለም ፈጣሪያችሁና አባታችሁ፥ ካህናችሁና ንጉሣችሁ እግዚአብሔር አብ፥ የዘለዓለም እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ አገራችሁና ንግሥታችሁ ድንግል ማርያም ነን።

"እናንተ ደግሞ፡ ለእኛ፡ ከመለኮታዊው አካላችንና ባሕርያችን ከፍለን፥ በአዳም አብራክና በሔዋን ማሕፀንም፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ ፈጥረንና አጥምቀን የወለድናችሁ፥ በክህነት የቀባናችሁና በነጋሢነት የሠየምናችሁ፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችን ናችሁ።

"እኛ፡ ለእናንተ፡ እንዲህ እንደመኾናችን፥ እናንተም፡ ለእኛ፡ እንዲህ እንደመኾናችሁ፡ እኛ፡ እናንተን፡ በመልካም የምናያችሁና የምንይዛችሁ፥ የምናስብላችሁና የምንሳሳላችሁ፥ የምንወድዳችሁና የምንራራላችሁ፥ የምንመግባችሁና የምንንከባከባችሁ፥ የምናሳድጋችሁና የምንጠብቃችሁ፥ የምናስተምራችሁና የምናሳውቃችሁ፥ የምንመራችሁና የምናስተዳድራችሁ፥ የምናጸናችሁና የምናኖራችሁ፥ አስፈላጊና ተገቢም ሲኾን፡ በወላጅነት ፍቅር የምንቆጣጠራችሁና የምናስጠነቅቃችሁ፥ የምንገሥፃችሁና የምንቀጣችሁ፡ እንደሕፃናት ተቀብለናችሁ ነው።

"እናንተ፡ በሥጋ የወለዳችኋቸውን ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁን፡ በእኩልነት እንደምታይዋቸውና እንደምታደርጉላቸው ኹሉ፡ እኛም፡ ከእናንተ በሚበልጥና መሥፈርቱ፡ ወሰን በሌለው መጠን፡ እናንተን፡ ወንዶቹንም፥ ሴቶቹንም ልጆቻችንን፡ በእኩልነት አይተን፡ 'ለእናንተ፡ በጎውን ኹሉ እናደርግላችኋለን!' ማለት ነው።

"ይህንም እውነታ፡ በትስብእት የተገለጸው መለኮታዊው ልጃችን መሢሕ ኢየሱስ፡ እንደእናንተ፡ እርሱን አምነውበት የተከተሉት ደቀ መዛሙርቱ፡ ወደእርሱ ቀርበው፡ 'መኑ እንጋ የዐቢ በመንግሥተ እግዚአብሔር?

"'በእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከኹላችን የሚበልጥ ማነው?' የሚል ጥያቄን ባቀረቡለት ጊዜ፡ እንዲህ ሲል በሰጣቸው መልሱ ገልጾታል። 'ወጸውዐ ሕፃነ፤ ወአቀሞ፡ ማእከሎሙ፤ ወይቤ፡ «አማን እብለክሙ፡ እመ ኢተመየጥክሙ፥ ወኢኮንክሙ ከመ ዝንቱ ሕፃን፡ ኢትበውኡ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር። ወዘአትሐተ ርእሶ፡ ከመ ዝንቱ ሕፃን፡ ዝ ውእቱ ዘየዐቢ፡ በመንግሥተ እግዚአብሔር።

"'አንድ ሕፃንን ጠርቶ፡ በመካከላቸው አቆመና፡ «እውነት እላችኋለሁ! በንስሓ ካልተመለሳችሁ፥ የእየራሳችሁን አስተሳሰብም፡ በእግዚአብሔር ደግነት፥ እውቀትና እውነት በማስተካከል፡ እንደዚህ ሕፃን ካልኾናችሁ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት አትገቡም። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ከኹሉ የሚበልጠው፡ ራሱን፡ እንደዚህ ሕፃን፡ ዝቅ የሚያደርገው ነው።»'"

ኪዳናዊ ወንድሜ! አንተንና እኔን የመሰለ አንድ ሰብኣዊ ፍጡር፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት፡ በእውነት የሚፈልግ ከኾነ፡ ከዚህ የቀለለና የበለጠ፡ "የምሥራች!" የሚያሰኝ፡ ከቶ ምን ሌላ ነገር ይኖራል? አይኖርም። ይኸውም፡ ራስን፡ ሕፃን ማድረግን ነው።

እንዲህ ከኾነ፡ እዚህ ላይ፡ "ትልቅ ከኾኑ በኋላ፡ ሕፃን መኾን፡ እንዴት ይቻላል?" የሚል ጥያቄ፡ በውስጣችን ይነሣሣ ይኾናል። ከተነሣሣብን፡ እንደአይሁዳዊው ኒቆዲሞስ ካልኾን በቀር፡ መልሱ፡ አንተም፥ እኔም፥ ኹላችንም፡ በእየራሳችን፡ በቀላሉ ልንመልሰው የሚቻለን ይመስለኛል። ይኸውም፡ እያንዳንዳችን፡ ሕፃን ስለነበርን፥ ዛሬም፡ በሰውነት ያስገኘናቸው ሕፃናት ልጆች ስላሉን፡ "ሕፃን መኾን፡ እንዴት ይቻላል?" ለሚለው ጥያቄ፡ ትክክለኛውን መልስ መስጠት ይቻለናል።

ከዚህ ቀደም እንዳስታወስሁህ፡ እስኪ አንተ እና እኔ፡ ለአንዲት አፍታ፡ እየራሳችንን፡ በወላጅነታችን ቦታ እናስቀምጥና፡ እንኳንስ፡ ገና በሕፃንነት ዕድሜ ያሉትን ቀርቶ፡ እየራሳቸውን፡ ወደሕፃንነት ሊመልሱ ያልቻሉትን፡ ትልልቆችና የሸመገሉትን ልጆቻችንን ጨምረንም ቢኾን፡ በዚያ ትልቅነታቸውና ሽምግልናቸው፡ በፈጣሪያቸው ላይ የሚፈጽሙት የክህደት ጥፋት ካልኖረ በቀር፡ የቱንም ያህል ቢበድሉን፡ "በፍጹም ይቅር አልላቸውም!" ብለን፡ እስከመጨረሻው የምንጨክንባቸው ይኖራሉን? አይመስለኝም።

እንግዴህ፡ በዚህ ረገድ፡ እግዚአብሔር፡ በአብነቱ፡ ማለትም፡ በአባትነቱ እና በእም፡ነቱ፡ ማለትም፡ በድንግል ማርያም እናትነቱ፡ እያንዳንዱን፡ ሰብአዊ ፍጡሩን፡ ወንዱን፡ "ሕፃን ልጃችን ነው!"፥ ሴቷንም፡ "ሕፃን ልጃችን ናት!" ብሎ፡ ኹለቱንም፡ በእኩል የሕፃንነት ደረጃና ፍቅር ተቀብሏቸው፥ እንደሚያኖራቸው የምናምን ከኾነ፥

እነዚሁ ልጆቹ፡ የሚያደርጉትን፡ ማናቸውንም ዓይነት ጥፋት ኹሉ፡ "የሕፃን ሥራ ነው!" ብሎ የሚያየውና የሚያልፈው፥ እንዲያውም፡ ክፋትና ተንኰል በሌለበት፡ በሕፃንነት ንጽሓ ባሕርይ ስላደረጉት የሚደሰትበት ከኾነ፥

እኒሁ ልጆቹም፡ እየራሳቸውን፡ ወደንጹሑ የሕፃን ደግነት በመመለስ፡ ክፋት፥ ሓሰትና ጥፋት በሌለበት ሕፃናዊ አስተሳሰብ ኾነው፡ ማናቸውንም ድርጊት፡ በቅንነት እንዲፈጽሙት፡ ከፈጣሪያቸው የተፈቀደላቸው መኾኑን ያወቁ ከኾኑ፡

ታዲያ! በዚህ ዓለም፡ ለሰው፡ ከዚህ የበለጠ፡ የሚያስፈነድቅና "የምሥራች!" የሚያሰኝ፡ ምን ደስታና ሀብት አለ? በእርግጥ የለም! ሊኖርም አይችልም።

፪. እዚህ ላይ፡ ሊወሳ የሚገባው፡ ሌላ ታላቅ ምሥራች ደግሞ አለ፤ ይኸውም፡ ሰው የኾነው የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ መሢሕ፡ በምድር ላይ እየተመላለሰ ሣለ፡ አብዛኛውን ጊዜ፡ ዐብሮአቸው ይውል የነበረው፥ በአንድ የማዕድ ገበታም ላይ ተቀምጦ፡ ይበላና ይጠጣ የነበረው፡ በአይሁድ ዘንድ፡ "ርኵሶችና ኃጢአተኞች" በተባሉት፥ እየራሳቸውንም፡ "አዎን! እንዲሁ ነን!" ብለው፡ ይህንኑ ምንነታቸውን በተቀበሉት ወገኖች መካከል እንደነበረ ይታወቃል።

ከዚህ የተነሣ፡ እነዚያ አይሁድ፡ ደቀ መዛሙርቱን፡ "ለምንት፡ **ምስለ መጸብሓን፥ ወኃጥኣን፡ ይበልዕ ሊቅክሙ?"**

ማለትም፡ **"መምህራችሁ፡ ከቀራጮችና ከኃጢኣተኞች ጋር ዐብሮ ስለምን ይበላል?"** ብለው በጠየቋቸው ጊዜ፡ ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ ጥያቄያቸውን ሰምቶ፡ የሰጣቸውን መልስ፡ አንተም፡ ኪዳናዊ ወንድሜ ታስታውሰዋለህ።

ያም፡ እንዲህ የሚለው ቃሉ ነው፡- **"ሕሙማን ይፈቅድዎ ለዐቃቤ ሥራይ፤ ወአኮ ጥዑያን። ሑሩ! ወአእምሩ፡ ምንት ውእቱ ዘይቤ፡ 'ምጽዋተ አበድር እመሥዋዕት!' እስመ ኢመጻእኩ፡ እጸውዕ ጻድቃነ፤ አላ ኃጥኣነ ለንስሓ።"**

ማለትም፡ **"ሓኪምን የሚፈልጉት፡ ሕመምተኞች እንጂ፡ ጤናማዎች አይደሉም። ነገር ግን፡ ኺዱ! 'ለእኔ ከምታቀርቡልኝ መሥዋዕት ይልቅ፡ ለሰው፡ በጎ ምግባርን ብታደርጉ እወድዳለሁ!' የሚለው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ ምን እንደኾነ እወቁ! እኔም፡ ወደዚህ ዓለም፡ ሰው ኾኔ የመጣሁት፡ ኃጢአተኞች፡ ከሓሰት ወደእውነት፡ በንስሓ እንዲመለሱ ልጠራቸው እንጂ፡ ጻድቃንን፡ ልጠራ አልመጣሁም!"** (ማቴ. ፱፥ ፲-፲፫።)

እግዚአብሔር፡ ሰው የኾነበትና ወደዚህ ዓለም የመጣበት ብቸኛ ዓላማ፡ ምን እንደኾነ፡ እነሆ፡ ራሱ፡ በግልጽ ተናገረ። ያ ዓላማ ምንድር ነው? ዓላማውማ፡ "ሕመምተኞች፥ ወይም፡ ኃጢአተኞች ናቸው!" ተብለው የተወገዙትን፥ እነርሱም፡ "አዎን! ነን!" ብለው፡ አምነው የተቀበሉትን ጎሥቋላዎች፡ እርሱ፡ እውነተኛ ሓኪማቸው ኾኖ፡ ባቀረበው ፍቱን የንስሓ መድኃኒትነት፡ ሊፈውሳቸው፥ አንጽቶም፡ ለጤናማ ጻድቃንነት ማብቃት ነው።

በሓኪም ሕክምና፡ "ልድን እችላለሁ!" ብሎ አምኖ፡ ወደሥጋዊው ሕክምና ቤት የሚኼደው በሽተኛ፡ እሓኪሙ ዘንድ የሚቀርበው እንደታመመ፡ ከነሕመሙ ሲኾን፡ ሊድንም የሚችለው፡ በሓኪሙና ሓኪሙ በሚሰጠው መድኃኒት አምኖ፡ በታዘዘለት ሕክምና፡ በትክክል ሲጠቀም መኾኑ ይታወቃል።

እንደዚሁ ኹሉ፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ፡ እውነተኛው ሓኪም የኾነው፡ መሢሕ ኢየሱስ፡ በዚህ መለኮታዊ ቃሉ መሠረት፡ በአንተ ጥያቄ ውስጥ የተካተቱትን፡ እነዚያን ኃጢአተኞች የተቀበላቸውና የሚቀበላቸው፥ በመካከላቸው ተገኝቶና በገበታቸውም ዙሪያ ዐብሮአቸው ኾኖ፡ ማዕዳቸውን የሚሳተፈው እኮ፡ ገና፡ ከነኃጢኣታቸው እንዳሉ መኾኑ፡ እንዲህ፡ በእውን ሲረጋገጥ፡ ታዲያ! ይኼ፡ ሌላው ምሥራች አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ።

የሰማዩ አባታችንና የሰማይዋ እናታችን፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ ለሰው የለገሡት፥ በፍጡር ቃል ሊገለጽ የማይቻል፡ ይህ፡ የፍቅር ጸጋና በአንደበት ሊነገር የሚያዳግት፡ ይህ የምሥራች መልእክት፡ በተለይ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች በኾኑት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ዘንድ፡ ምን ዓይነት አቀባበልና አፈጻጸም ሊኖረው እንደሚገባ፡ እዚህ ላይ መግለጹ የሚያስፈልግ አይደለም። ይህ እውነታ፡ በእነርሱ ዘንድ ታውቆና ታምኖበት፡ በተግባር ላይ መዋሉ እየቀጠለ የሚገኝ፡ ዋና ተልእኳቸው ነውና። ስለዚህ፡ ምሥራቹ ይቀጥላል።

ነገር ግን፡ እዚህ ላይ፡ "ምሥራቹ!" ስንል፡ ምን ማለታችን ነው? መምህራችንና መሪያችን፡ መሢሕ ኢየሱስ፡ **"ሑሩ ውስተ ኵሉ ዓለም! ወስብኩ ወንጌለ፡ ለኵሉ ፍጥረት! ...ወናሁ! አነ እሄሉ ምስሌክሙ፡ በኵሉ መዋዕል፣ እስከ ኅልቀተ ዓለም።"**

ማለትም፡ **"ወደዓለሙ ኹሉ ኺዱ! ምሥራቹንም፡ ለፍጥረት ኹሉ ዐውጁ! ...እነሆ! እኔ፡ እስከዓለሙ ፍጻሜ ድረስ፡ ኹልጊዜ፡ ከእናንተ ጋር እኾናለሁ።"** ብሎ፡ ለሓዋርያቱና ለደቀ መዛሙርቱ፥ ዛሬም፡ ለእኛ፡ ለኪዳናውያትና ኪዳናውያን የነገረን፡ "ምሥራቹ!" ምንድር ነው? (ማር. ፲፮፥ ፲፭። ማቴ. ፳፰፥ ፳።)

ምሥራቹማ፡ "የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጆች" ኾነው፡ በታማኝነታቸው ጸንተው ከቀጠሉት፡ ከጥቂቶቹ በቀር፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ጥንትም፥ ኋላም፥ በመጨረሻውም ዘመን፡ በጎ ላደረገለት፥ ለዘለዓለምም፡ ይኽን በጎነቱን አጽንቶ ለቀጠለለት ፈጣሪው፡ ምን ኾኖ፥ ምንስ አድርጎ እንደተገኘ የሚገልጸው እውነታ ነው።

ይኸውም፡ ውለታቢስ፥ ተቃዋሚውና ጠላቱ ኾኖ መገኘቱ ሲኾን፡ ይኸው የተበደለው ፈጣሪ ግን፡ እንዲህ አድርጎ የበደለውን፡ ይህንኑ ፍጡሩን፡ በዚህ ኹኔታውና አቋሙ እንዳለም እንኳ ቢኾን፡ <u>የሚያየውና ተቀብሎ የሚያኖረው፡ እንደሕፃን ልጁ የመኾኑ፡ የምሥራች ዜና ነው።</u>

አዎን! ይህንኑ ፍጡር፡ ቸሩ ፈጣሪው፡ በእግዚአብሔር አብ፡ አባትነቱ፥ በእግዚአብሔር እም፡ እርሷም፡ ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም፡ እናትነቷ፥ በእግዚአብሔር ወልድ ልጅነቱ እና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እውነትነቱ፡ በመጀመሪያ፡ እንደዚያ በመልኩና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ብሎ በሥነ ፍጥረት አስገኝቶ መውለዱ፡ ታዲያ! ለምንድር ነው?

ቀጥሎም፡ ይኸው ሰብአዊ ፍጡሩ፡ ከተቃዋሚው፡ ከክፉው መንፈሳዊ ፍጡር ጋር፡ ግብረ ዐበር ኾኖ በመጥፋቱ፡ እርሱን ፈልጎ ለማግኘትና ለማዳን፡ ወደር የሌለውን ተጋድሎን አካኺዶ፥ ራሱንም፡ ለሕማማተ መስቀል መሥዋዕትነት በማቅረብ፡ የቤዛነት ዋጋን መክፈሉ፡ ታዲያ! ለምንድር ነው?

በመጨረሻም፡ ጥንቱኑም፡ ለዚሁ፡ ሰብአዊ ፍጡሩ፡ ሰጥቶት የነበረውን፡ መንፈስ ቅዱሳዊ ጸጋውን፡ አኹን ደግሞ፡ በበለጠ መጠን አትረፍርፎ ማበርከቱ፡ ታዲያ! ለምንድር ነው?

ይህንኑ "ምሥራች!" ለመላ ፍጥረቱ ለማስገኘት አይደለምን? ፍጥረቱንስ በሙሉ፡ ለዚህ ባለምሥራችነት፥ ለዚህ ሕፃንነት ለማብቃት አይደለምን? አዎን! በእርግጥ ነው እንጂ።

እንዲያ ከኾነ፡ ታዲያ! ያን ኹሉ፡ የፈጣሪ ቸርነት፥ ያን ኹሉ መለኮታዊ ተጋድሎ፥ ያን የሚያህል፡ አምላካዊ መሥዋዕትነት፥ ያን የሚያህል ትስብእታዊ ቤዛነት መክፈል፥ ያን የሚያህል መንፈስ ቅዱሳዊ ጸጋን፡ በምልዓት ማፍሰስስ፡ ለምን አስፈለገ? እንዲያው ለመኾኑ፡ ይህን ኹሉ መለኮታዊና ትስብእታዊ ዋጋ፡ <u>*ከንቱ*</u> ልናደርገው ይገባልን? ፈጽሞ አይገባም።

ይህ ኹሉ የፍጹም ፍቅርና የልግሥና በረከት፡ ያስገኘውን መልካምና ዘለዓለማዊ የነጻነት ህልውና፡ በምስጋና ተቀብለን፡ በተለይ እኛ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ በእውን ሕይወት አድርገን ልንኖረውና ልንጠቀምበት፥ ሌሎችንም፡ ለዚህ ዕድል እንዲበቁ፡ በአገልግሎታችን መርዳት ይገባናል። አይመስልህም?

አዎን! ምሥራቹና የምሥራቹ ታላቅነት፡ ምናልባት፡ እየራሳችንን፡ "ኪዳናውያንና ኪዳናውያት" ብለን ለምንጠራና "ለዚያ ሕይወት በቅተናል!" ለምንል፡ ለአንዳንዶቻችን፡ ይህን ያህል ላይሰማን ይችል ይኾናል። አንተ ኪዳናዊው ወንድሜ፡ ምንነታቸውንና ማንነታቸውን ዘርዝረህ ላቀረብሃቸው፡ ለእነዚያ ወገኖች ግን፡ እንዲህ አይደለም። ምሥራቹ፡ ከእኛ ይልቅ፡ በይበልጥ፡ ለእነርሱ፡ ታላቅነቱ እንደሚሰማቸው፥ ደስም እንደሚያሰኛቸው፡ ከቶ አልጠራጠርም። ምሥራቹ፡ በእርግጥ፡ ለእነርሱ ነውና። ይህን፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ በፍጹም እምነት ልናገር፡ ቅዱሱ ኪዳን ያስችለኛል፤ ያስደፍረኛልም።

ምንነታቸውንና ማንነታቸውን ዘርዝረህ ያቀረብሃቸውን፥ የእነዚያን ደካሞች ሰዎች ሥራዎች፡ አንተ፡ ኪዳናዊው ወንድሜ፡ ለኪዳናዊነት በመብቃትህ ምክንያት፡ "አላደርጋቸውም!" ትል ይኾናል። መልካም ብለሃል፤ አዎን! አታደርጋቸውም።

እንግዲያ፡ የእኛ፡ የኪዳናውያንና የኪዳናውያት ካህናት ተልእኮ፡ ምንድር ነው? እኒያ ደካሞች ወንዶችና ሴቶች፡ በንስሓ ተመልሰው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን ለመቀበል ፈቃደኛ ይኾኑ ዘንድ፡ ዕድሉን ማቅረብ፥ መንገዱንም ማሳየት አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ። ደግሞስ፡ እነርሱ፡ በዚህ ዕድል ለመጠቀም ከቻሉ፡ እኛ ለምንገኝበት፡ ለዚያ፡ ለኪዳናዊው የኢትዮጵያዊነት ሕይወት፡ እነርሱም ይበቁ ዘንድ መርዳት፡ የተልእኳችን ዓላማ ሊኾን አይገባውምን? አዎን! በእርግጥ ይገባዋል።

በእነርሱ፡ በደካሞቹ በኩል ግን፡ በዚህ ዕድል ለመጠቀም ፈቃደኛ ካልኾኑና ካልቻሉ፡ የምሥራቹ ጸጋ፡ በእነርሱ ላይ መሥራቱ እንደሚቀጥል አምነን፡ ይህንኑ የምሥራቹን ዜና፡ በጆሮአቸው እንዲሰሙት በማድረግ፡ የተልእኳችንን ዓላማ፡ ከግቡ ለማድረስ፡ በተግባራችን ልንጸና አያስፈልገንምን? አዎን! ያስፈልገናል እንጂ።

በዚህ ጊዜ፥ ወይም፡ ይህ በሚኾንበት ጊዜ፡ ያ የምሥራቹ ጸጋ፡ እርሱም፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እነዚያን ደካሞች፡ እንደእውነተኛው ኪዳናዊ እና እንደእውነተኛዪቱ ኪዳናዊት፡ ማሰብን፥ መናገርንና ማድረግን እንዲጀምሩ፡ የእውቀቱን ኃይል ሰጥቶ፡ ከጨለማው የእንቅልፍ ኑሮአቸው ይቀሰቅሳቸዋል፥ ያነሣሣቸዋል፤ ያንቀሳቅሳቸዋል፤ ይመራቸዋል፤ ለወጣኒነቱም ማዕርግ አብቅቶ፡ መልካሙን፡ የሥጋ፥ የነፍስና የመንፈስ ሕይወታዊ የዕድገት ጕዞ፡ በፍጹም ነጻነት፥ በእውነትና በብርሃን፥ በእምነትና በሰላም፥ በፍቅርና በደስታ፥ በእየራሳቸው ይቀጥሉ ዘንድ ይለቅቃቸዋል።

## መደምደሚያ

እንግዴህ፡ ኪዳናዊ ወንድሜ፡ ፈቃደ ሥላሴ ሆይ! በዚህ ርእሰ ነገር ላይ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ይህ ኹሉ ከተነገረ፥ ከተጻፈም በኋላ፡ ውጤቱ፡ አኹንም፡ ምናልባት፡ እንደሚጠበቀው፡ መልካሙ ፍሬያማነት ሳይኾን ቢቀር፡ በእኔ በኩል የማበረክትህን፡ የቀረችኝን፡ አንዲቱን መክሊት መጽሔት እንዳቀርብልህ ፍቀድልኝ! እርሷም፡ አንተን፡ ለአንዲት አፍታ፡ ነቢዩን ቅዱስ ዳዊትን አድርጋ የምታሳይህ ተልእኮዬ ናት።

ባለፈው፡ የማብራሪያ ደብዳቤዬ ላይ እንዳወሳሁት፡ እግዚአብሔር፡ "**ረከብክዎ ለዳዊት ገብርየ፤ ብእሴ ምእመነ ዘከመ ልብየ፤ ዘይገብር ኵሎ ፈቃድየ።**"

ማለትም፡ "**አገልጋዬን፡ ዳዊትን አገኘሁ፤ እርሱ፡ እንደልቤ የኾነ፡ የታመነ፥ ፈቃዴንም ኹሉ የሚያደርግ ሰው ነው።**" ብሎ የተናገረለት፡ ይኸው ነቢዩ ዳዊት፡ በታማኝ አገልጋዩ፡ በኢትዮጵያዊው ኦርዮ ላይ የፈጸመው የግፍ ግፍ በደል፡ ለዚች ተልእኮዬ፡ አብነት ኾና የቀረበችበት ምክንያት አለ።

አዎን! ብዙ ሚስቶች ያሉት፡ የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት፡ የኦርዮን፡ አንዲት የሕግ ሚስቱን ቀምቶ ማግባቱ ሳይበቃው፡ በጦር ሜዳ ላይ እንዲገደል ማድረጉ፡ በፈጣሪው ፊት፡ ታላቅ ኃጢአት ኾኖ በመገኘቱ፡ በዚህ ክፉ ሥራው፡ እግዚአብሔር አዝኖ፡ የቅጣቱን ፍርድ፡ በራሱ፡ በዳዊት አስፈርዶ፡ ያስፈጽም ዘንድ፡ ነቢዩ ናታንን፡ ወደእርሱ እንደላከ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረውን ዜና መዋዕል ታውቀዋለህ።

ይኸው ነቢይ፡ በዚሁ ንጉሥ ፊት ቀርቦ፡ ኦርዮን፡ አንዲት በግ ብቻ ባለችው ደሀ መስሎ፥ ራሱን፡ ዳዊትንም፡ አያሌ የከብት መንጋዎች ባለው ባለጠጋ መስሎ ባቀረበለት የበደልና የግፍ ዝክረ ነገር፡ "የራሱ ብዙ በጎች እያሉት፡ የዚያን የደሀውን አንዲት በግ አሳርዶ ለእንግዳው ያቀረበው፡ ያ ባለጠጋ መገደል አለበት!" ብሎ፡ ራሱ ዳዊት በፈረደው ፍርድ፡ ራሱ፡ የቅጣቱ ተቀባይ ኾኖ መገኘቱና በንስሓ የተሻሻለው ቅጣት እንደተፈጸመበት፡ ይህንም እውነታ ታስታውሰዋለህ።

አንተ እና እኔ፡ እየተወያየንበት ባለው፡ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ፡ አኹን፡ እየኾነ ያለው፡ እውን ኹኔታ፡ ይኸው መኾኑን፡ ኪዳናዊ ወንድሜ፡ በራስህ ተመልከተው! በዚህ ጊዜ፡ እንዲህ የሚል የመንፈስ ቅዱስ መልእክት፡ በኪዳናዊው መንፈስህ ውስጥ ሠርፆ ይሰማሃል፡- «ያን፡ "እንዲህ አስቧል፤ እንዲህ ተናግሯል፤ እንዲህም አድርጓል!" ያልከውን ሰው፡ እስኪ፡ ለአንዲት አፍታ፡ "እኔ ራሴ ነኝ!" ብለህ ራስህን አድርገው፤ ራስህ ኹነው! በዚህ ጊዜ፡ በራስህ ላይ፡ ራስህ፡ ፍርድህን ስጥ! ፍርድህንም፡ ራስህ ተቀበል! ያ ሰው አንተ ነህና። ያ ሰው፡ አንተ ከኾንህ፡ ምንድር ነው የምታደርገው? ማድረግ የሚገባህን፡ አውቀህ ታደርጋለህ ማለት ነው።

«በቃ! በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠርህበትና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾንህ!" በተባልህበት አምላካዊ ሥልጣንህና ኃይልህ ተጠቅመህ፡ ያን አድርግ። አለቀ። በዚያን ጊዜ፡ እንደዳዊት፡ ንስሓ መግባት ቢያስፈልግህ፡ በንስሓህ ንጻና፡ እንደእርሱ፡ እንደቅዱስ ዳዊት፡ ኪዳናዊነትህን አጽንተህ፡ እውነተኛው ኢትዮጵያዊ፡ የቅዱሱ ኪዳን ባለቤት ኹን!

«"አይ! እኔ ንጹሕ ነኝ። ንስሓ አያስፈልገኝም!" ካልህ ደግሞ፡ መልካም! ያን ደካማ ኃጢአተኛ፡ ቢያስፈልግህ፡ በመለኮታዊው የምሥራቹ ዐዋጅ ተጠቅመህ፡ ለንስሓና ለመጨረሻው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት አብቃው! አለቀ። ይኸው ነው።

«"በኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡- አንደኛ መጽሓፍ፡ "እኔ፡ ማነኝ!"፥ በኹለተኛውም መጽሓፍ፡ "ባልንጀራዬ፡ ማነው?"፥ በሦስተኛውም መጽሓፍ፡ "እግዚአብሔር፡ ማነው?" የሚሉት መልእክቶች ኹሉ የሚያመለክቱት፡ ይህንኑ እውነት መኾኑን አትዘንጋ፤ እነዚህና እነርሱን የመሰሉት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥር ታትመው የተሠራጩት፡ የቅዱሱ ኪዳን መጻሕፍት ኹሉ የሚያተኩሩትም ወደዚሁ እውነት ነውና።»

በመጨረሻም፤ በመጠይቃዊው ደብዳቤህ መዝጊያ ላይ፡ "ታናሽ ልጅህ" ብለህ የሠነዘርኸው ቃል፡ ከፍቅርህና ከትሑት ልቦናህ የፈለቀ መኾኑን ባውቅም፡ አንጻራዊ ምሳሌን በማቅረብ፡ ከላይ ለጠቀስሁት፡ ላላወቅኸው ምንነትህና ማንነትህ፡ አንድ ማስረጃ ሊኾን፥ ከዚህ የተነሣም፡ ለፍጹሙ ኪዳናዊነትህ፡ ገና፡ ጥቂት የቀረህ ሃይማኖታዊ ምግባር መኖሩን የሚያሳይ ምልክት ሊኾን፥ በይበልጥም፡ የአንተንም፥ የእኔንም ኪዳናዊ የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንን፡ ወደጥያቄ አስገብቶ፡ ለጥርጣሬና ለግብዝነት የሚዳርገን ፍንጭ ሊኾን እንደሚችል መገመቱ፡ ለአንተም ቢኾን የሚያዳግትህ አይኾንም።

እንኳንስ አንተ፡ በመንፈስና በጽሑፍ ብቻ ያገኘሁህና ያወቅሁህ ቀርተህ፡ በመልኩ ለፈጠራቸው እግዚአብሔር፡ ባለአደራው ኾኜ እንዳሳድጋቸው፡ ከእኔ ከአዳምና ከባለቤቴ ከሔዋን፡ በሰውነት የተገኙት ወንዶችና ሴቶች እንኳ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች እና የኢትዮጵያ ድንግል ማርያም ልጆች" ናቸው እንጂ፡ የእኔ ልጆች አይደሉም፤ አይባሉምም፤ የእነርሱ አባታቸው፡ እግዚአብሔር፥ እናታቸውም፡ ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም ናቸው።

ከዚህ የተነሣ፡ አንተም፥ እኔም፥ እነርሱም፥ ሌሎቹም፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፥ የቀረውም ሰብኣዊ ፍጡር ኹሉ፡ ቢያውቀውም፡ ባያውቀውም፥ ቢቀበለውም፡ ባይቀበለውም፥ ቢያምንበትም፡ ባያምንበትም፡ በእግዚአብሔር በኩል የኾነውና የተደረገው ፍጹም ቸርነት፡ ኹላችንም፡ በእግዚአብሔር አባትነት እና በኢትዮጵያ ድንግል ማርያም እናትነት፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ የእነርሱ፡ የእውነተኞቹና ዘለዓለማውያኑ ወላጆቻችን፡ ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች የመኾናችን እውነታ ነው።

ስለዚህ፡ እባክህ፡ ኪዳናዊ ወንድሜ! እንግዴህ ወዲህ፡ እንዲህ ዓይነቱ ነገር እንዳይደገም ታደርግ ዘንድ፡ በቅዱሱ ኪዳናችን ዋቢነት፡ በጥብቅ አደራ እልሃለሁ። ለዚህ፡ ለአኹኑም ግብርህ፡ የግል ንስሓህን እንድትፈጽም አስታውስህ ዘንድ ፍቀድልኝ!

ማብራሪያዬን፡ የምደመድመው፡ ከዚህ በሚከተሉት፡ የአድናቆትና የምርቃት ቃላት ይኾናል፡- መንፈስ ቅዱስ፡ በአንተ፡ በኪዳናዊ ካህኑ (አገልጋዩ) ላይ ዐድሮ፡ "ሰዎች" ለተባልንና በማናቸውም ዓይነት ሃይማኖት ለምንገኝ፡ ወንዶችና ሴቶች፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያዊ/ዊት"፥ "ዐምሓራ"፥ እና/ወይም፡ "ክርስቲያን" ተብለን ለምንጠራ፥ ይልቁንም፡ "ኪዳናውያንና ኪዳናውያት 'የእግዚአብሔር ልጆች' እና 'የኢትዮጵያ ልጆች' ነን!" ለምንል ኹሉ ጭምር፡ ለእያንዳንዳችን፡ እየተናገረና እያደረገ ያለው፡ መለኮታዊ መልእክት አለው።

ይኸውም፡ "'እኔ፡ እንዲህ ነኝ!' ብዬ፡ ራሴን፡ ለራሴ፥ ለእግዚአብሔርና ለሰው ኹሉ፡ በይፋ ባሳወቅሁትና ላሳወቅሁት ምንነቴና ማንነቴ፡ ፩ደኛ፡ እውነተኛ ነኝን? ወይስ፡ ሓሰተኛ፥ ውሸታምና አስመሳይ? ፪ተኛ፡ታማኝ ነኝን? ወይስ፡ ከሃዲ፥ ወረተኛና አታላይ? ፫ተኛ፡ የጸናሁ ነኝን? ወይስ ግብዝ፥ አስጠቂና ልፍስፍስ?" ብለን፡ እየራሳችንን በመመርመርና በመጠየቅ፡ ለእየራሳችን መልስ እንድንሰጥ ነው።

ስለዚሁ መንፈስ ቅዱሳዊ ድንቅ ሥራ፡ የአድናቆት ምስጋናዬን፡ ለሠሪው፡ ለእግዚአብሔር እያቀረብሁ፡ አንተንም፡ ኪዳናዊ ወንድሜን፡ "እንኳን ለዚህ ተልእኮ ለመመረጥ አበቃህ!" እያልሁ ደስታዬን በመግለጽ፡ መርቄሃለሁ።

እንግዴህ፡ አንተም፥ እኔም፥ ኹላችንም ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ **"አንትሙሰ፡ ኩኑ ፍጹማነ፤ ከመ አቡክሙ ሰማያዊ፡ ፍጹም ውእቱ!"**

ማለትም፡ **"የሰማዩ አባታችሁ፡ ፍጹም እንደኾነ፡ እናንተም፡ እንደርሱ፡ ፍጹማን ኹኑ!"** ለሚለን ለፈጣሪያችንና ለአምላካችን፥ ለአባታችንና ለመሪያችን፥ ለመምህራችንና ለመድኃኒታችን፥ ለካህናችንና ለንጉሣችን፡ መሢሕ ኢየሱስ መለኮታዊ ቃል፥

ደግሞ፡ **'ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ!'**

ማለትም፡**"ልጄ፡ የሚላችሁን ኹሉ፡ ስሙት! አድርጉትም!"** ለሚለው፡ ለቅድስት እናቱና እናታችን፥ ለቅድስት ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም፡ ማሕየዊ ቃል፡ እየራሳችንን ልናበቃ ይገባናል!" ብዬ፡ በማሳሰብ፡ ማብራሪያ ጽሑፌን አቆማለሁ።

በሰላመ እግዚአብሔር አብ እና በፍቅረ እግዚአብሔር እም፡ ከኪናዳዊው ቤተሰብህ ጋር፡ በደኅና ኹን!

*ታኅሣሥ ፳፩ ቀን፥ ፳፻፲ ዓመተ ምሕረት።*

ኪዳናዊ ወንድምህና ክህነታዊ ባልደረባህ፡-
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልድ-ኢየሱስ።